**ደደቢት ብድር እና ቁጠባ ተቋም አ/ማ**

# የ ቦርዱ የ2024/25 የሒሳብ ዓመት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት

ሰኔ 30/2025

**መቐለ**

# ይዘት


I. ሳመሪ ሪፖርት (Summary Report)....2

1. መግቢያ....3

2. ቁልፍ መደብ የተያዙ ግቦች እና አፈፃፀማቸው....4

2.1. የአቅም ግንባታ መደቦች አፈፃፀም 4

3. የአበይት በደቦች አፈፃፀም....4

3.1. የ ኦፕሬሽን መደቦች አፈፃፀም 4

*3.1.1. ብድር አሰጣጥ....4*

*3.1.2. ብድር ማስመለስ የሚመለከት....5*

*3.1.3. የውዝፍ ንፅፅር ከባለፈው የበጀት ዓመት ሰኔ 30/2024....6*

*3.1.4. ቀሪ ብድር በሚመለከት....7*

*3.1.5. ቁጠባ በሚመለከት....7*

*3.1.6. የዲጅታል ግልጋሎት....7*

*3.1.6.1. ተሌ ብር አግልጋሎት....7*

3.2. የአይቲ መደቦች አፈፃፀም እና የ ኮር ባንኪንግ ሲስተም ማስፋፋት 9

*3.2.1. የኮር ባንኪንግ ሲስተም ቴክኒካል ድጋፍ የሚመለከት....9*

3.2.2 የአይቲ ኢንፍራስትራክቸር መደቦች.......10

*3.2.3. የአይቲ ሴክዩሪቲ ስራዎች በሚመለከት.... 11*

3.3. የኮርፖሬት ሰርቪስ መደቦች አፈፃፀም 12

*3.3.1. የፋይናንስ የመመለከት....12*

*3.3.2. የንብረት ግዢና አስተዳደር የሚመለከት....16*

*3.3.3. የኢንጂነሪንግ መደቦች.... 17*

*3.3.4. የሰው ሃይል መደቦች አስተዳደር.... 17*

3.4. በዋና ስራ ፈፃሚ ስር የሚገኙ የስራ ክፍሎች የስራ አፈፃፀም 19

*3.4.1. እቅድ ፣ ጥናት እና የቢዝነስ ማበልፀግ.... 19*

*3.4.2. ሚድያ፣ ህትመትና የማስተዋወቅ ስራዎች.... 20*

*3.4.3. የሪስክ እና ኮምፕሊያንስ ስራዎች....20*

*3.4.4. የሕግ አገልግሎት....20*

*3.4.5. የውስጥ ኦዲት....21*

*3.4.6. ግልጋሎትና የደንበኞች ደህንነት ጥበቃ ክፍል.... 22*

4. እንደ ተቋም የነበረን ጠንካራና ደካማ ጎኖች.... 22

*4.1. ጠንካራ ጎን....22*

*4.1.2. ደካማ ጎን....22*

*4.1.3. የመፍትሄ ሓሳቦች....22*

5. በእቅድ ተይዘው ያልተፈፀሙ መደቦች....23

6. በሚቀጥለው 2025/26 ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች....23

6. አባሪ....23

## I. ሳመሪ ሪፖርት (Summary Report)

ደደቢት የብድር እና ቁጠባ ተቋም አ/ማ ካላት 218 ቅርንጫፎች እና ን/ቅርንጫፎች በዚህ በጀት ዓመት በደቡባዊ ዞን ወደ ስራ የገቡ 7 ጨምሮ በስራ ያሉት ቅርንጫፎችና ን/ቅርንጫፎች 183 (84%) ሲሆኑ የተቀሩትን 35 (16%) ግን ከግዝያዊ መስተዳድሩ ስር ውጭ የሚገኙ በመሆናቸው ከስራ ውጭ ሁነው ይገኛሉ። ዋና ቢሮ፣ ዞን እና ቅርንጫፎችን ጨምሮ ከጠቅላላ 226 ( ሳተላይት ጨምሮ) ቅርንጫፎች እና ን/ቅርንጫፎች 205 (91%) የኮር ባንኪንግ ሲስተም አስገብቶው በኔትዎርክ የሚሰሩ ናቸው። የተቀሩት 19 ከቁጥጥር ውጭ ያሉት ናቸው።

እንደ ተቋም እስካሁን ያለን ቋሚ ሰራተኛ ብዛት 3,435 ከዚህ 43% ሴቶች ሲሆኑ ኮንትራት ቅጥር ደግሞ 48 ከዚህ 4% ሴቶች ናቸው ። የተቋማችን ግዚያዊ እና ቋሚ ሰራተኞች ድምር 3,483 ሲሆኑ ከዚህ 42% ሴቶች ናቸው።

የቁጠባ መደብ አፈፃፀም በሚመለከት በዚ በጀት ዓመት 280,913 አዳዲስ ቆጣቢ ደንበኞች የቆጠቡ ሲሆን በጠቅላላ 1.864 ሚልዮን የአካውንት ብዛት ያላቸው (Account holder) አሉ። በገንዘብ መጠን ሲታይ በሰኔ 2024 የነበረ ብር 13.915 ቢልዮን ድምር ቁጠባ (Ballance) በብር 2.2 ቢልዮን በዚ በጀት ዓመት በመጨመር አሁን ያለው ቀሪ ቁጠባ ብር 16.117 ቢልዮን ሊሆን ችሏል። ይህ ከባለፈው በጀት ዓመት ሰኔ 2024 ሲነፃፀር ጠቅላላ ቁጠባ ተቋማን በ16% ጭማሪ ሊያሳይ ችሏል።

ብድር መስጠት በሚመለከት በዚ በጀት ዓመት ውስጥ ለ18,061ደንበኞች ብር 3.770 ቢልዮን የተሰጠ ሲሆን ፍፃሜ ከእቅድ ሲነፃፀር በሰው 26% በገንዘብ ደግሞ 38% ብቻ ነው የተፈፀመው ። ብድር ማስመለስ ሲታይ ደግሞ ብር 4 ቢልዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ የነበረ ሲሆን አፈፃፀሙ ብር 3.275 ቢልዮን ሊመለስ ችሏል ። ይህ በፐርሰንት ሲገለፅ 82% ነው። የቀሪ ውዝፍ ብድር መጠን ሲታይ በሰኔ 2024 የነበረ መጠን ውዝፍ ብር 5.075 ቢልዮን ሲሆን በዚህ በጀት ዓመት ግን ወደ ብር 3.908 ቢልዮን ሊወርድ ችሏል። አብዛኞዎቹ የብድር ዓይነቶች ውዝፋቸው በመቀነስ የሚገኝ ሲሆን ሌሎች የተወሰኑ የብድር አይነቶች ግን የውዝፍ መጠናቸው በመጨመር ይገኛሉ። በተቋም ደረጃ በብሄራዊ ባንክ የተሰጠ ማተካከያ መሰረተ በሰኔ 2024 መጨረሻ የነበረ የጠቅላላ ሃብት መጠን 11.96 ቢልዮን ሲሆን ቀሪ ብድር 11.16 ቢልዮን ነው ። በመጨረሻ ሰኔ 2025 ያለ ጠቅላላ የሃብት መጠን 18.77 ቢልዮን ሲሆን ቀሪ ብድር ብር 10.97 ቢሊዮን ሊሆ ችሏል። ይህ በንፅፅር ሲገለፅ የተቋሙ ጠቅላላ ሃብት ከባለፈው ዓመተ ሰኔ/2024 በዚ በጀት ዓመት በብር 6.81 ቢልዮን ሲጨምር ቀሪ ውዝፍ ደግሞ በብር (0.19) ቢልዮን ሊቀንስ ችሏል። በአጠቃላይ ተቋማን በዚህ በጀት ዓመት ብር 0.394 ቢልዮን በትርፍ ላይ እንዳለ ሊያሳየን ችሏል። ስለዚህ እንደ ተቋም በሚቀጥለው በጀት ዓመት ሰፊ ርብርብ በማረግ የብድር ዕድል እንዲሰፋና ያሉን ውዝሮች እንዲመለሱ ትልቅ ጥረት ማድረግ የሚያስፈልግ ይሆናል።

## 1. መግብያ

ደደቢት የብድር እና ቁጠባ ተቋም አ/ማ በትግራይ ታሪክ ጀማሪ የማይክሮፋይናንስ ተቋም መሆኗ የሚታወቅ ነው። የማክሮፋይናንስ ጀማሪ እንደመሆኗ በትግራይ የነበረ የፋይናንስ እጥረት እና የስራ አጥነት ችግር በመፍታት ግምባር ቀደም ናት። ይሁን እንጂ ከጥቅምቲ 2013 ዓ/ም እስከ ሕዳር 2015 ዓ/ም በተካሄደ ጦርነት እንደተቋም ትልቅ የሃብት ውድመት አጋጥሟታል።

ይህ ያጋጠመ ውድመት ከፕሪቶርያ የተኩስ አቁም የሰላም ስምምነት በኋላ እንዲ ጠና በማድረግ ቀላል ጉዳት የደረሳቸው ቅርንጫፎ የሪከቨሪ እቅድ በመዘጋጀት ወደ ስራ እንዲ ገቡ ተደርጓል። ከዚህ በመነሳት የ 2015/16 ዓ/ም እቅድ በማዘጋጀት ባለፈው ዓመት ወደ ስራ ገብተን ሰፊ ስራ ተሰርቷል። በተለይ ተቋማችን ባደረገው የወለድ ምህረት መሰረት በማረገ በውዝፍ ማስመለስ 99% በመፈፀም የተሻለ ኣፈፃፀም የነበረ ሲሆን ቡብድር መስጠት ደግሞ ከ 50% በላይ ሊፈፀም ተችሏል። የኮርባንኪግ ሲሰተም ማፋፋት ሲታይ ደግሞ ባለፈው ዓመት 112 ዞናልና ዋና ቢሮን፣ ቅርንጫፎች እና ን/ቅርንጫፎች ሲስተም በመጠቀም ግልጋሎት ሊሰጥ ችሏል። በሌሎች መደቦችም በደንብ በመስራት ተስፋ ሰጪ ውጤት ሊገኝ ችሏል።

ስለሆነም በዚህ የበጀት ዓመት 2016/17 /2024/25 የባለፈው ዓመት እንደመነሻ በመውሰድና የነበሩትን ድክመቶች እና ጥንካሬዎች በመለየት እና እንደ መደብ በማካተተ ትላልቅ መደቦች ለመፈፀም እቅድ በማዘጋጀት ወደ ሚመለከተው በማቅረብ እንዲፀድቅ በማድረግ ወደ ስራ ገብተናል።

በዚህ መሰረት ጠቅላላ የ 2016/17 2024/25 በጀት ዓመት የስራ አፈፃፀም ስራ እንደሚከተለው ቀርቧል።

- የዚህ ሪፖርት ባለቤት፡- ደደቢት የብድር እና ቁጠባ ተቋም አ/ማ ቦርድ
- ሪፖርቱ በተመለከተ አጭር ማብራርያ ፡- ይህ ሪፖርት የቦርዱ የ 2016/17 /2024/25 በጀት ዓመት እቅድ እና አፈፃፀም በማነፃፀር የቀረበ ሪፖርት ነው።
- የሪፖርቱ ዓላማ፡- የ2016/17 በጀት ዓመት መደቦች የስራ አፈፃፀም በእቅድ አንፃር የሚያመላክት ሲሆን ከዚህ የተገኙ ድክመቶች ለማስተካከል እና ጥንካሬዎችም በማስፋት ለቀጣይ ውጤታማ ስራ ለመስራት ያለመ ነው።
- የሪፖርቱ ወሰን፡- ይህ ሪፖርት የ 9 ክፍሎችን (Departments) 6 በዋና ስራ አስፈፃሚ ስር የሚገኙ ግልጋሎት ሰጪ የስራ ዘርፎች የስራ ሪፖርት የሚያጠቃልል ነው ።

## 2. ቁልፍ መደቦች የተታቀዱ ግቦች እና አፈፃፀማቸው

2.1. የዓቅም ግንባታ መደብ አፈፃፀም ፡-ይህ መደብ የውስጥ ተቋም እና ከተቋም ውጭ የሚሰጡ ስልጠናዎች /የአጭር እና የረጅም ግዜ ስልጠናዎች/ የሚመለከት ሁኖ ባለሙያዎች እና አመራሮች ያላቸውን የመፈፀም አቅም ክፍተት በመሙላት የአገልግሎት አሰጣጥ ስርአት ከፍ ለማድረግ ነው። በዚህ መሰረት የተሰጡ ስልጠናዎች እንደሚከተለው ቀርቧል።

- ✔ በውስጥ እና በውጭ ባለሞያዎች የተሰጠ ስልጠና በድምር 3,503 ሰራተኞች በኮርባንኪንግ ፣ የፋይናንስ ስራዎች ፣ ERP ሞጅል፣ ድጅታል ሰርቪስ ፣ መሰረታዊ የኮምፒተር ስልጠና ፣ የብድር ትንተና ፣ የህግ ባለሙያዎች የልምድ ልውውጥ እና ገምገማዊ ስልጠናዎች፣ ስጋት እና የማጭበርበር ወንጀሎች በመከላከል፣ ክትትልና ግምገማ ፣ የማነቃቃትና የስራ ባህል ለመነቃቃት

የስልጠና እቅድ የተያዘ ሁኖ አፈፃፀሙ ደግሞ ለ 2067 ሰራተኞች ከነዚህ 605 ሴቶች የሆኑ ስልጠና ሊሰጥ ችሏል። ከባለፈው የበጀት ዓመት 2015/16 ሲነፃፀር በ 72% ቅናሽ ሊያሳይ ችሏል። የዚህ ቅናሽ ዋናው ምክንያት የገንዘብ እጥረት በመኖሩ ነው።

## 3. የዓበይቲ መደቦች አፈፃፀም

### 3.1. የኦፕሬሽን መደቦች አፈፃፀም

#### 3.1.1. ብድር መስጠት

- ✔ በዚህ በጀት ዓመት ብድር ለ 70,000 ደንበኞች ብር 10 ቢሊዮን እንዲታደል እቅድ ተይዞ ለ18,061 ደንበኞች ብር 3.770 ቢልዮን ሊሰጥ ተችሏል። ይህ ከባለፈው በጀት ዓመት 2015/16 የተሰጠ ብድር ሲነፃፀር በዚህ በጀት ዓመት በ5% መጠን ብድር ሊቀንስ ችሏል። በሌላ በኩል በተበዳሪዎች ብዛት ሲታይ ደግሞ በዚህ በጀት ዓመት ለ 70,000 ደንበኞች ብድር እንዲሰጥ እቅድ ተይዞ አፈፃፀሙ ሲታይ ደግሞ ከተያያዘው እቅድ 25.8% የተሰጠ ሲሆን ፤ ይህ ከባለፈው በጀት ዓመት 2015/16 ሲነፃፀር በ34% ሊቀንስ ችሏል። የዚህ አፈፃፀም መቀነስ ምክንያት ሁሉም ቅርንጫፎቻችን ወደ ስራ ይገባሉ ብለን እቅድ ይዘን በመኖራችንና ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ወደ ስራ አለመግባታቸው ነው፣ ከተባባሪ አካላትና መንግስት በትብብር ይሰራ የነበረ ወደ ስራ ባለመግባቱ (የከ/ፓኬጅ፣ ገ/ፓኬጅን ተዛዋዋሪ ብድር)፣ ቁጠባ እንደሚፈለገው አለመሰብሰብ፣ የጥሬ ገንዘብ እጥረት በመኖሩ እና ውዝፍ ብድር በሚፈለገው መጠን አለመመለሱን በብድር መስጠት አፈፃፀማችን ቅናሽ ሊያሳይ ችሏል።
- ✔ በዚህ በጀት ዓመት በተወሰኑ የተመረጡት የብድር ዓይነቶች እንደ መደበኛ ፣ እሙን ፣ ቢዝነስ ፣ ደመወዝተኛ ፣ ቤት መስርያ ፣ ወዴፕ ፣ አውድ ፣ ሰራተኛና የፕሮጀክቶች ብድር በተወሰነ እንቅስቃሴ የተሰራ ነው።
- ✔ የተቋማችን የብድር ሁኔታ ሲታይ ትልቁ ቢዝነስ ስለሆነ ለዚህ በሚያጠናክሩ በስፋት ማለትም ውዝፍ ብድር ማሰመለስና ቁጠባ አሁነ ካለው በእጥፍ መስራት፣ አሁን እንደተጀመረው ከተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተለያዩ ውሎች በማሰር እና በመጫረት ያለን የገንዘብ እጥረት በመቅረፍ የደንበኞቻችን ፍላጎት ለሚሟላት የብድር እድል ለማስፋት በሚቀጥለው የበጀት ዓመት ትኩረተ የሚያስፈልገውና ሊሰራለት የሚገባ ጉዳይ ነው።

#### 3.1.2. ብድር ማሰመለስ የሚመለከት

ሰንጠረዥ**1፡-** የተመለሰና ቀሪ ውዝፍ ንፅፅር በጀት ዓመት 2016/17 ከባለፈው በጀት ዓምት 2015/16

| መደብ | የተመለሰ በቢልዮን ብር 2015/16 ዓ/ም | | የተመለሰ በቢልዮን ብር 2016/17 ዓ/ም | |
|---|---|---|---|---|
| | የተመለሰ | ቀ/ውዝፍ | የተመለሰ | ቀ/ውዝፍ |
| እቅድ | 3 | 2.404 | 4 | 1.5 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፍፃሜ | 2.977 | 5.075 | 3.275 | 3.908 |
| ጭማሪ እና ቅናሽ | | | 10% | 23% |

- ✔ በዚህ በጀት ዓመት ብድር ለመመለስ የተያዘ እቅድ ብር 4 ቢልዮን ሲሆን ተቋማችን ባደረገው የወለድ ምህረትና ሌሎች ማትግያዎች እንዲሁም የሰራተኛው ጥረት ተጨምሮበት አፈፃፀሙ ብር 3.275 ቢልዮን ብድር ሊመለስ ችሏል። ይህ ከባለፈው በጀት ዓመት 2015/16 አፈፃፀም ሲነፃፀር የዚህ በጀት ዓመት አፈፃፀም በ 10% ጭማሪ ሊያሳይ ችሏል።
- ✔ የተሻለ የተመለሰ የብድር መጠን ያላቸው የብድር ዓይነቶች ስናይ በ ቢዝነስ ፣ ቤት መስርያና መደበኛ ብድር ሊሆኑ ችሏል ።
- ✔ በዞናል ቅርንጫፎች ደግሞ መቐለ፤ እንዳስላሰና ኣክሱም የተሻለ ብድር የተሰበሰባቸው ሲሆኑ ከጠቅላላው የተመለሰ ብድር ሲታይ መቐለ 34% ፣ እንዳስለሰ 16% እንዲሁም ኣክሱም 15% መጠን ድርሻ አላቸው።
- ✔ በእቅድ አፈፃፀም አንፃር ከ100% በላይ የፈፀሙ ዞናል ቅርንጫፎች ስናይ ዓብይ ዓዲ፣ ኣኩሱምና እንዳስላሰ ሲሆኑ መቐለ ደግሞ 100% ልትፈፅም ችላለች። ይህ በእንደዚህ እያለ ዞናል ዓድግራት 93% ፣ ዞናል ማይጨው በስራ ላይ ያሉ ጨንፈሮች መሰረት በማድረግ የሰራው 92% ፣ ዞናል ኲሓ ደግሞ 80% የእቅዳቸው ሊፈፅሙ ችሏል። ስለሆነም በተለይ ዞናል ኹሓ በቀጣይ ሰፊ ስራ መስራት የሚያስፈልጋት ስትሆን ዞናል ዓዲግራትና ማይጨው ደግሞ ቀጣይ ስራዎች በትኩረት መስራት ያስፈልጋል።
- ✔ በዚህ በጀት ዓመት ከእቅድ አንፃር ዝቅተኛ የብድር አመላለስ አፈፃፀም ያላቸው ስናይ ደግሞ ሊዝ (12.75%) ፣ ተዘዋዋሪ (16.56%) ፣ ዋስትና ፈንድ (45.55%) እንዲሁም ገ/ፓኬጅ (48.25%) ሊሆኑ ችሏል።
- ✔ በቀሪ ውዝፍ በኩል ሲታይ በዚህ በጀት ዓመት የተያዘ እቅድ ብር 1.5 ቢልዮን ሲሆን ፍፃሜ ደግሞ ብር 3.908 ቢልዮን ቀሪ ውዝፍ ብድር ሊሆን ችሏል። ይህ ከባለፈው በጀት ዓምት 2015/16 ሲነፃፀር በ 23% ቀሪ ውዝፍ ብድር ሊቀንስ ችሏል።
- ✔ ቀሪ የብድር ውዝፍ ጭማሪ ያሳየበት ምክንያት በ8% ወለድ ለወጣቶች የተሰጠ ብድር ኣብዛኛው ስራ ላይ ባለመኖሩ የተወሰነ ደግሞ የመክፈል ፍላጎት ባለመኖሩ ሊከፍል ባለመቻሉ ነው ፣ ናሙና ወስዶ አለመክሰስ፣ ትላልቅ ተበዳሪ ድርጅቶች ብድራቸው ሊመልሱ ባለመቻላቸው ነው።

**3.1.3.** የውዝፍ ንፅፅር ከባለፈው በጀት ዓመት ሰኔ **2015/16**ዓ/ም ጋር ሲታይ

- ✔ ባለፈው ዓመት ሰኔ ወር የነበረ ውዝፍ ብር 5.075 ቢልዮን የነበረ ሲሆን በዚህ በጀት ዓመት ያለን ውዝፍ ሲታይ ብር 3.908 ቢልዮን ሊሆን ችሏል። ከባለፈው ዓመት ሰኔ 2015/16 ዓ/ም አፈፃፀመ ሲነፃፀር የዚህ በጀት ዓመት በ 23% ውዝፍ ሊቀንስ ችሏል። ከዚህ በተጨማሪ ባለፈው ዓመት ሰኔ 2015/16 ዓ/ም ወደ ውዝፍ ገብተው የነበሩት ደንበኞች ብዛት 212,608 የነበረ ሲሆን በዚህ በጀት ዓምት በ 25% ሊቀንስ ችሏል። ከዚህ ሪፖርቱ እንደሚያሳየን ውዝፍና ወደ ውዝፍ ገብተው የነበሩት ተበዳሪዎች እየቀነሰ እየሄደ ያለና የተሻለ ሲሆን ግን ደግሞ ከዚህ በላይ መሻሻል ያለበት ነው።
- ✔ በዚህ በጀት ዓመት የውዝፍ ጭማሪ ያሳዩ የብድር ዓይነቶች የሴቶች ያለ ማያዣ፣ እሙን ደንበኛ ፣ ቴክኖሎጂ ማባዛት ፣ አውድ ፣ የሰራተኛ ብድር እና ሊዝ ናቸው።

### 3.1.4. ቀሪ ብድር በሚመለከት

ሰንጠረዥ 2፦ ንፅፅር ቀሪ ብድር 2016/17 ዓ/ም ምስ ዝሓለፈ 2015/16 ዓ/ም

| መደብ | የቀሪ ብድር መጠን በቢልዮን ብር 2015/16 ዓ/ም | | የቀሪ ብድር መጠን በቢልዮን ብር 2016/17 ዓ/ም | |
|---|---|---|---|---|
| | በብር | የቀሪ ተባዳሪ ብዛት | በብር | የቀሪ ተባዳሪ ብዛት |
| እቅድ | 13.999 | 532,174 | 17.436 | 375,546 |
| ፍፃሜ | 11.166 | 301,226 | 10.977 | 183,714 |
| ከ በጀት ዓመት 2015/16 ያለ ጭማሪ /ቀነስ% | | | -1.69 % | -39% |

✔ በዚህ በጀት ዓመት እንደተቋም እንዲኖረን የተያዘው ቀሪ ብድር እቅድ 17.436 ቢሊዮን ሲሆን ፍፃሜ ደግሞ ብር 10.977 ቢሊዮን ቀሪ ብድር ሊሆን ችሏል ። የቀሪ ብድር መጠን ከባለፈው 2015/16 ዓ/ም ጋር ሲነፃፀር በዚህ በጀት ዓመት በ 1.69% ቅናሽ ሊያሳይ ችሏል። በሌላ በኩል ቀሪ ተበዳሪዎች ሲታይ እቅድ የሰው ብዛት 375,546 ሲሆን ፍፃሜ በሰው 183,714 ሲሆን ይህ ከባለፈው የበጀት ዓመት 2015/16 ሲነፃፀር በ39% ሊቀንስ ችሏል። ስለዚህ በዚህ በጀት ዓመት በ 183,714 ደንበኞ እጅ ብር 10.977 ቢሊዮን እንዳለ አይተናል ። ስለዚህ በቀጣይ ስራችን በቀሪ ብድር በእጥፍ መስራት እንደሚያፈልግ ነው።

### 3.1.5. ቁጠባ በሚመለከት

✔ በቁጠባ አገልግሎት ላይ በዚህ በጀት ዓመት አዲስ ቁጠባ 4.4 ቢልዮን እንዲቆጠብ እቅድ ተይዞ ፍፃሜው ብር 2.2 ቢልዩን ወይም 50% ከእቅዱ ነው። የዚህ ደካማ አፈፃፀም ምክንያት የተባባሪ አካላት አስፈላጊ ድጋፍ አለማደረግ እና ከባንኮች በመመሳጠር ቁጠባ እንዲወጣ ማድረግ ስለታየ ነው። በሌላ መልኩ ካለፈው በጀት ዓመት 2015/16 ጋር ሲነፃፀር ፍፃሜ ቁጠባ በ166% ቁጠባ የጨመረ ሲሆነ ከባለፈው ዓመት ሰኔ ወር /2015/16 እንደተቋም በ 16% ሊጨምር ችሏል። እንደዞኖች ስናይ ደግሞ ያለውን ቀሪ ቁጠባ በመያዝ ተጨማሪ ቁጠባ በመሰብሰብ በሁሉም ዞኖች የተሻለ እንኳ ቢሆንም የተሻለ አፈፃፀም ያሳዩ ከ 200 ሚልዮን በላይ መቐለ ብር 1.1 ቢልዮን ፣ ሰ/ምዕራብ ብር 0.335 ቢልዮን እንዲሁም ማእከላይ ዞን ብር 0.222 ቢልዮን ቀሪ ቁጠባ ሊጨምሩ ችሏል።

✔ በቆጣቢዎች በኩል ሲታይ ደግሞ 395,312 ደንበኞች እንዲቆጥቡ እቅድ ተይዞ ፍፃሜ 280,913 ሊሆኑ ችሏል። ይህ ከባለፈው በጀት ዓመት 2015/16 ፍፃሜ ቆጣቢዎች ሲነፃፀር በዚህ በጀት ዓመት በ 6% የቆጣቢዎች ብዛት ሊቀንስ የቻለ ሲሆን ጠቅላላ የቆጣቢዎች ብዛት እንደተቋም ደግሞ በ 17% ሊጨምር ችሏል።

✔ እንደተቋም ደግሞ እስከ እዚህ በጀት ዓመት የቆጣቢዎች ብዛት 1.937 ሚልዮን ያሉት ሲሆነ የቁጠባ መጠናቸው ደግሞ ብር 16.11 ቢልዮን ሊደርስ ችሏል።

### 3.1.6. ግልጋሎት ዲጅታል

#### 3.1.6.1. የተሌ ብር አገልግሎት ግልጋሎት

- ✔ በዚህ በጀት ዓመት በ196 ቅርንጫፎች ግልጋሎት ቴሌ ብር ለመጀመር እቅድ ተይዞ በ 161 ቅርንጫፎች ዋና ቢሮ ጨምሮ ስራ እንዲጀምሩ የተደረገ ሲሆን ይህ ከእቅዱ 82% ሊፈፀም ችሏል። የተቀሩት 35 በ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ እንዲሁም ደቡብ ትግራይ የሚገኙ ቅርንጫፎቻችን ወደስራ ስላልገቡ ነው።
- ✔ በዚህ በጀት ዓመት በቴሌ ብር በተደረገ የገንዘብ ዝውውር ገቢ ብር 488.8 ሚልዮን ሲሆን በሰው ደግሞ 116,164 ወጪ ቡብር 25.9 ሚልዮን በሰው 5,948 ከወጪ ቀሪ ብር 462.9 ሚልዮን በሰው 110,216 ከዚህ ስራ ወደ ተቋም ገቢ የተደረገ ኮምሽን ደግሞ ብር 933,975.67 ሊሆን ችሏል።
- ✔ በዚህ በጀት ዓመት አዳዲስ የቴሌ ብር ደንበኞች ብር 2,030 የተመዘገቡ ሲሆን በጠቅላላ ያሉን ድምር ደንበኞች 5,073 ሊሆን ችሏል።

#### 3.1.6.2. ኤም ብር የሚመለከት

- ✔ በዚህ በጀት ዓመት ያልተወራረደ ሒሳብ የነበራቸው ለ 30 ኤጀንት ብር 655,813.37 እንዲከፈሉ ተደርጓል።

#### 3.1.6.3. ሳፋሪኮም

- ✔ ተቋማችን ከፋሪኮምጋር ለመስራት በገባው ስምምነት መሰረት በዚህ በጀት ዓመት 155 ቅርንጫፎች ግልገሎት M-PESA ለመጀመር እቅድ ተይዞ ፍፃሜው 37 ቅርንጫፎች ግልጋሎት ሊጀምሩ ችሏል ። የተቀሩት ቅርንጫፎች በየአከባቢያቸው የሳፋሪኮም ማስፋፍያ ኔትወርክ ባለመጀመሩ ነው።
- ✔ 60 የሳፋሪኮም ሞባይል በእርዳታ የተገኘ ሲሆን 26 ቅርንጫፎች መቐለ ፣ ደቡብ 11 እንዲሁም ዋና ቢሮ 2 እንዲሰጣቸው በማድረግ ስራ የጀመሩ ሲሆን የተቀሩት 21 ሞባይል ደግሞ ስቶር ላይ ይገኛል ይህ በገንዘብ ሲተመን 420 ሺህ የሚሆን በእርዳታ ሊገኝ ተችሏል። እንዲሁም ከ ሳፋሪኮም ለስራ ማስጀመርያ የሚሆን በኣድቫንስ ኤለክትሮኒክስ ገንዘብ ብር 3 ሚልዮን እንዲሰጠን ቃል የተገባልን ሲሆን በዚህ በጀት ዓመት 1 ሚልዮን ገቢ ተደርጎ ወደ ስራ ገብተናል። እስካሁን ስራ በጀመሩት ብር 355,742 ገቢ የተደረገ ሲሆን ብር 108,685 ወጪ በማደረግ ብር 1,421.35 ኮምሽን ልናገኝ እለናል።

### 3.1.7. የተለያዩ ክፍያዎች መፈፀም በተመለከተ

- ✔ ተቋማችን ከ ማረት ጋር ባደረገው አብሮ የመስራት ውል ለ18,000 ተረጂዎች ብር 210 ሚልዮን ክፍያ የተፈፀምመ ሲሆን በፕሮግራሙ የታቀፉ 18,000 ደንበኞች የአዲስ ቡክ መክፈቻ በያንዳንዱ 50 በማስከፈል በድምር ከባቢ ብር 900,000 በቁጠባ መልክ የተገኘ ሲሆን ከነዚህ 18,000 ተረጂ ደግሞ የትራንስፈር ክፍያ ብር 270,000 ሊገኝ ችሏል።

### 3.1.8. ኢንሹራንስ የሚመለከት

- ✔ የህይወት መድን ግልጋሎት (credit life insurance ) በዚህ በጀት ዓመት ብድር ከሚወስዱ ተበዳሪዎች ደንበኞች 55,155 ብር 83.4 ሚልዮን ክፍያ /premium / ለመሰብሰብ እቅድ ተይዞ ፍፃሜው ሲታይ ብር 29.2 ሚልዮን ሲሆን በሰው ደግሞ 12,257 ሊሆን ችሏል ።
- ✔ ካሳ ክፍያ በዚህ በጀት ዓመት ለ 185 ተበዳሪዎች በሞት ለሚለዩ ብር 16.68 ሚልዮን እንዲከፈል በእቅድ ተይዞ ፍፃሜ ሲታይ በሞት ለተለዩ 103 ደንበኞች ብር 8.06 ሚልዮን ካሳ የህይወት መድህን ሊከፈል ችሏል።

- ✔ የሰራተኞች መድን (self staff life insurance) በዚህ በጀት ዓመት የአካል ጉዳት 24 ፣ ሞት 28 በድምር ለ 52 ሰራሕተኞች ለጉዳት ብር 1.43 ሚልዮን ለሚሞቱ ሰራተኞች ብር 2.56 ሚልዮን በድምር ብር 2.99 ሚልዮን የመድን ኢንሹራንስ የተተያዘ ሁኖ ፍፃሜ የአካል ጉዳት 8 ሰው ብር 946 ሺህ ብርተከፍሏል፤ በሞት ለተለዩ 7 ሰዎች ብር 2.64 ሚልዮን የተከፈለ ሲሆን በድምር ለ15 ሰው ብር 3.59 ሚልዮን ለሰራተኞች ካሳ ተከፍሏል።

**3.1.9.** የደንበኞች አገልግሎት በሚመለከት

- ✔ እንደ ተቋም የደንበኞች አገልግሎት ትኩረት እያገኘ እየሄደ ያለና በዚህ ረገድ ከነበረው የተሻሻለ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። በዚህ በጀት ዓመት የተነሱ ቅሬታዎች ስናይ የተቃጠለ ደብተር የሚመለከት የተቃጠለ ዶኩሜንት የ ኮርባንኪንግ እና ኢንተግሪቲ ጉዳይ የ ጀነሬተር ፣ የተፈናቀሉ ቆጣቢዎች ወደ ሲስተም አለመግባት ፣ ሲስተም ሲቆም ደንበኞች መጉላላት የመሳሰሉ ችግሮች ነበሩ። ስለዚህ የቅሬታቸው ጉዳይ በየግዜው በመፈተሽ ማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ እና እንዳስፈላጊነቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በመስጠት በደንበኞች አያያዝ ላይ ለውጥ ማምጣት ይገባል።

**3.2.** የኣይቲ መደቦች አፈፃፀም እና የኮር ባንኪንግ ሲስተም ማስፋፋት

**3.2.1.** የኮር ባንኪንግ ሲስተም ቴክኒካል ድጋፍ የሚመለከት

- ✔ የኮርባንኪንግ ሲስተም ማስፋፋት በቅርንጫፎች እና ንኡስ ቅርንጫፎች የተሰራ ሲሆን በተለይ አዳዲስ ቅርንጫፎች በመክፈት ሰፊ ስራ ተሰርቷል።
- ✔ በዚህ በጀት ዓመት 89 ቅርንጫፎችና ንኡስ ቅርንጫፎች ዳታ የማጥራት እና ወደ ሲስተም እንዲገቡ መደረጉ።
- ✔ 8 ንኡስ ቅርንጫፎች ከግዝያዊ አስተዳደሩ ውጭ ስለሆኑ በእንዳስላሴ ከተማ ሁነው ወደ ሲስተም እንዲገቡ ተደርጓል።
- ✔ ኮር ባንኪንግ ሲስተም ገብቶላቸው ዳታ ማይግሬት ያላረጉ ጨንፈሮች እና ንኡስ ጨንፈሮች ዳታው እንዲጠራ እና ወደ ሲስተም እንዲገባ የ ስቴጂንግ ኤርያ ስራዎች በሰፊው ተሰርቷል።
- ✔ የነበሩት ኢሹዎች በሰባት ተከፍለው ስራ የተጀመረ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ተሰርተው ወደ ዋና ሲስተም የሚገቡት ዩኤንሲ ኢሹ ተብለው የነበሩት 133 አሬንጅመንት፣ ቢል ኢን ነጋቲቭ ሁነው የነበሩት 31፣ አልዘጋ ብለው የነበሩት /አን ኤብል ቱ ክሎዝ/ 14 ፣ ሪቨርሳል 24 እንዲሁም ኢኤ ሳስፐንስ ተሞክሮ መፍትሄ ሊገኝ ተችሏል።
- ✔ በአጠቃላይ የ ኮርባንኪንግ ስራዎች ሲታይ ወደ ሲስተም የገቡ ቅርንጫፎችና ንኡስ ቅርንጫፎች ዞናል እና ዋና ቢሮ ጨምሮ 205 እንደደረሰ፣ ሙሉ በሙሉ ዳታቸው ገብቶ በሲስተም የሚሰሩ 204፣ ዳታ ያልገባላቸው አንድ (ማይፀብሪ)፣ በሳተላይት የሚሰሩ 2፣ ከቁጥጥር ውጭ የሆኑ 19 ከነዚው ወደ ሲስተም የገቡ 8 ሊሆኑ ችሏል።

**3.2.2.** የኣይቲ ኢንፍራስትራክቸር ደገፍና ክትትል

- ✔ የ ኔትወርክ DMZ ዞን ለ ዲጅታል ቴክኖሎጂ ስራዎች በቀላሉ እንዲሰራና የሙከራ ስራዎች እንድንሰራ የሚያስችለን ወሳኝ የ ኔትዎርክ አንድ አአካል በመሆኑ ከዚህ ጋር ተያይዞ ደግሞ በዳታሰንተር ኔትዎርክ የማሻሻል ስራዎች እንዲሰሩ ተደርገዋል።

- ✔ የ ቪፒኤን አገልግሎት መፍትሄ እንዲያገኝ በማድረግ በቂ የሆነ ቪፒኤን እንዲዘጋጅ እና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት /ቬንደሮች/ እንዲጠቀሙ ተደርጓል።
- ✔ ኤስኤምኤስ፣ ዩኤስኤስዲ፣ ከ ኢትስዊች፣ ከ ይሙሉ ወዘተ ሊሰሩ የሚገባቸው ኮንፊገሬሽኖች እንዲሰሩ ተደርጓል።
- ✔ ኢንተርኔት በሁሉም ቅርንጫፎች ይገባ የነበረው አሁን ከ ዋና ቢሮ እንዲያገኝ በማድረግ ትልቅ ወጪ ሊቀንስ ችሏል።
- ✔ አዳዲስ በተጨመሩ ጨንፈሮች እና ንኡስ ጨንፈሮችየተለያዩ የ ቴሌ አገልገሎት በመጠቀም በ 7 አዳዲስ የ ኮፐር መስመር፣ 16 የ ቪፒኤን ሲም፣ 3 ደግሞ ቪሳት እንዲተከልላቸው በማድረግ ክትትል በማድረግ ወደ ስራ ገብተዋል።
- ✔ ወደ ቅርንጫፎች እና ንኡስ ቅርንጫፎች አዳዲስም ጨምሮ ወደ ሓዉዜን ፣ቆጎጋ ፣ ሮማናት ፣ ማይ መኸደን ፣ ዓ/ዓዲ ነጂሓ ፣ ሳሪስ ፣ 22 ፣ ማረት ፣ ቤት ህንፀት ፣ ላጪ ፣ ኢንዳስትሪና ሌሎች የ ኔትዎርክ ማስፋፋት ስራዎች እንዲሰሩ ተደርገዋል።
- ✔ በ አይቲ ሳፖርት የተጠገኑ ኤሌክትሮኒክስ ስራዎች በ ዋና ቢሮ ብቻ ግምቱ ብር 4.1 ሚልየን በዚህ ዓመት ተሰርቷል።
- ✔ የ ዋና ቢሮና ቅርንጫፎች ኔትዎርክ ለመቆጣጠር የሚያስችል የ ፒአርቲጂ ሶፍትዌር እንዲገባ በማድረግ በዚህ በኩል ክትትል ለማድረግ ተችሏል።
- ✔ በአጠቃላይ ሲታይ የ ዳታ ኔትዎርክ የገባላቸው ዋና ቢሮ፣ ቅርንጫፎች፣ መሰልጠኛ ቦታዎች በተቋማችን የገባ ኔት ወርክ በመጨመር 179 ሊሆኑ ችሏል።
- ✔ በዋና ቢሮና ቅርንጫፎች በተለያዩ ቦታወች በነባሮች እና አዳዲስ የተሰሩት የኔትዎርክ ስራዎች በብር 1.7 ሚልዮን የሚገመት የተሰራ ሲሆን ይህ የተወሰኑት ቅርንጫፎች ሳይጨምር ነው።
- ✔ በ ዳታሰንተር ደግሞ ብር አንድ ሚልዮን የሚገመት የቅድመ ጥገናና ስራ ሊሰራ ተችሏል።
- ✔ አጋዥ ሶፍትዌር /ሄልፕ ዴስክ/ በ ዋና ቢሮ ያለ ሰራተኛ የሚያስፈልጉት የ ኣይቲ እገዛ መሳርያ ገብቷል።
- ✔ አክቲቭ ዳይሬክትሪ ለተቋም ባለው የ ሰኩዩሪቲ ጥቅም በፍጥነት ሊሰራ ስለሚያደርገው ከ ዩዘር መፍጠር ጀምሮ ሁሉም ሪሶርስ ወደዚህ እንዲገባ በማድረግ ትላልቅ ስራዎች እንዲሰራ ተደርጓል።
- ✔ ሃርመኒ ኢንድ ፖይንት ለተቋማችን ካልተፈለገ ቫይረስ የሚከላከል አንቲ ቫይረስ ስለሆነ ባለን ሁሉ ኮምፒተር የተጫነ መሆኑ።
- ✔ አዳዲስ ንብረቶች በሚገዙበት ግዜ ደግሞ ስፐሲፊኬሽን በማዘጋጀት ጀምሮ ተገዝቶ እስኪገባ ድረስ የማረጋገጥ ስራ ተሰርቶ ገቢ የሚደረግ መሆኑ።
- ✔ የተበላሹ የኤሌክትሮኒክስ ንብረት ተጠግነው ሊያገለግሉ የሚችሉና ሊወገዱ የሚገባቸውን በመለየት ከተቋሙ ኮሚቴ በመሆን ተሰርቷል።

### 3.2.3. የ ኣይቲ ሴኩሪቲ ስራዎች በሚመለከት

- ✔ የ ቼክ ፖይንት ሴኩሪቲ ሲስተም በተከታታይ 5 ቀኖች 16 ሰዓት በመስራት አመርቂ የሆነ የዲፕሎይመንት ስራዎች ሊሰራ ተችሏል። ወደተግባር እንዲገባና የተቋሙ ደህንነት እንዲጠበቅ ተደርጓል።
- ✔ 1,170 ኮምፒተሮች ወደ አንድ ዶሜይን እንዲገባ ቼክፖይንት ሃርመንይ ኣንቲቫይረስ ሊጫኑ ተደርገዋል።
- ✔ የ ኤዲኤል ሰኩዩሪቲ ኮንፊገሬሽን አሰራር ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ገብቷል።
- ✔ የሃርመኒ ኢንድ ፖይንት ማንዋል ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተገብተዋል።

- ✔ ከ ኮንሰልታንት በመሆን የ ኣይቲ ሰኩሪቲን ድጅታል ትራንስፎርሜሽን ስራዎች ጥብቅ ክትትል በማድረግና ዓቅም በመፍጠር ለቀጣይ በራሳችን ዓቅም ለመስራት በምያስችል መልኩ እየተሰራ ነው።
- ✔ የ ኢንተርኔት አጠቃቀም እንደ ተቋም በዋና ቢሮ ሁኖ ኮንትሮልድ ሊደረግ ፣የ ዩኤስቢና ሌሎች ፖሊሲዎችም እንዲተገበሩ ተደርገዋል።
- ✔ የ ሚድል ዌርና አንደኛ ፌዝ ኤፒኣይስ ስራዎች ተሰርቶ በተቋማችንም እንዲረጋገጥ ተደርጎ ወደ ዋና ፕሮዳክሽን ሰርቨራችን እንዲጫን ዝግጅት ተደርጓል።
- ✔ የ ሞባይል ባንኪንግና ዩኤስኤስዲ በተመሳሳይ ከ ኤፒኣይ እንዲሰራና በተደጋጋሚ እንዲሞከር በማድረግ ተዘጋጅቶ ይገኛል።
- ✔ የ ኮልሰንተር ስራዎች በተመሳሳይ ተሞክሮ ተዘጋጅቶ ይገኛል።
- ✔ ይህ ወደ ተግባር ለማስገባት የ ሰኩዩሪቲ ስራዎች በኮንሰልታት በማሰራት ላይ ይገኛል።

የተለያዩ ፕሮጀክቶች ስራዎች በሚመለከት

- ✔ የ ዲጂታል ስራዎች ለማስገባት የሚያግዙ ማንዋሎች እና ፕሮሲጀሮችን እንዲዘጋጁ ተደርገዋል።
- ✔ በ ሞባይል ባንኪንግ ፣ ዩኤስ ኤስ ዲ፣ ኤስ ኤም ኤስና ኮልሰንተር የ ቴክኒካልና ቢዝነስን ስልጠናዎች እንዲሰጥ ተደርጓል።
- ✔ የ ዲጂታል አገልግሎት በትግርኛም እንዲሰራ ተደርጓል፣ የሙከራ ስራዎችም አልቀዋል።
- ✔ የ ኢኣርፒ ፕሮጀክት ማንዋሎች የ ሪኩይርመንት ዶክመንት በየክፍሉ እንዲዘጋጅና እንዲስተካከል መደረጉ፣
- ✔ የ ሳይበር ሪዛይለንስና ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስራዎች በሚመለከት፡- የ ፕሮጀክት ቻርተር ስራዎች ዝርዝር የያዘ ዶኩመንት ተዘጋጅቶ እንዲፀድቅ መደረጉ።
- ✔ ለሳይበር ሪዛይለንስ ፣ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራተጂ የሚያስፈልግ ፍሬም ዎርክ ዶክመንቶች የተለያዩ ዎርክሾፖች በማካየድ ሊዘጋጁና ሊፀድቁ የተደረገ ሲሆን በዚህ መሰረት የተዘጋጁ ሳይበር ሪዚለንስ ማቹሪቲ ኣሰስመንት ፣ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ማቹሪቲ ኣሰስመንት፣ ኮምፒተንሲ ሞዴል ለሳይበር ሪዚለንስን ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ፣ የ ሳይበር ሪዚለንስን ዲጂታል ትራንስፎርሜሽንና ስትራተጂ ሮድማፕ ሊሰሩ ችሏል።

## 3.3. የኮርፖሬት ሰርቪስ መደቦች አፈፃፀም

### 3.3.1. ፋይናንስ በሚመለከት

- ✔ የሰራሕተኛ በየቀኑ የሚሰሩት እንደ አበል፣ ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም፣ ቅድመ ደሞዝ ፣ ቢዝነስ ኣድቫንስ ፣ ብድር ፣ የ ለቀቁ ሰራተኞች ዳረጎት ፣ የዓመት ዕረፍት ፣ ኣክቲንግና ትራንስፖርት አለዋንስ ድህረ ክፍያዎችና ሌሎች ዕለታዊ የተለያዩ ክፍያዎች ተሰርቷል።
- ✔ የንብረት ግዢና ህንፃ የተሟላ ሰነድ እንዲቀርብ በማድረግ በውል መሰረት ከብር 240 ሚልዮን በላይ እንዲሁም ዓመታዊ የሶፍቲዌር ማደሻ ብር 131 ሚልዮን ክፍያ ሊፈፀም ችሏል።
- ✔ በያንዳንዱ ቅርንጫፍ እና ንኡስ ቅርንጫፍ ያለ የገንዘብ ፍሰት ክትትል በማድረግ ብር 950 ሚልዮን የተሻለ የገንዘብ ፍሰት ካላቸው በመሰብሰብ እጥረት ወዳላቸው ቅርንጫፍ እና ንኡስ

ቅርንጫፍ ብር 860 ሚልዮን የገንዘብ ፍላጎት ባቀረቡት መሰረት የገንዘብ ዝውውር ሊደረግ ተችሏል። እንዲሁም ከ ዋና ቢሮ ለደንበኞች ብር 553 ሚልዮን በቀጥታ ትራንስፈር ሊደረግ ተችሏል።

- ✔ የተወሰነ በባንክ ያለው ገንዘብ የተሻለ ወለድ ለማግኘት በግዜ ገደብ እንዲቀመጥ በማድረግ የተሻለ ትርፍ በማግኘት ወለዱ ደግሞ አስቀድሞ በመሰብሰብ የተሻለ ትርፍ ሊገኝ ተችላል::
- ✔ ሳምንታዊ የገንዘብ ቁጥጥር በማካሄድ ያለን የገንዘብ መጠን ክትትል በማድረግ ሪፖርት እንዲቀርብ ተደርጓል።
- ✔ የቅርንጫፍና ንኡስ ቅርንጫፍ ቼክና ሲፒኦ ሲጠይቁ መስጠትና ከሲስተም ጋር መናበብ ተሰርቷል።
- ✔ በባንኮች አዲስ ሂሳቦች ሲከፈትና በተቋም በተለያየ ምክንያት የፈራሚዎች ለውጥ ሲዴረግ ማስተካከያ የሚደረግ መሆኑ:: እንዲሁም ኣዳዲስ ቅርንጫፎችና ንኡስ ቅርንጫፎች ሲከፈቱ በባንክ ሂሳብ እንዲከፈትላቸው ደብዳቤ የሚፃፍ መሆኑ::
- ✔ ለመንግስት ሊከፈል የሚገባው ገንዘብ ማለትም የስራ ግብር፣ የጥሮታና የንብረት ግዢ ዊዝ ሆልዲንግን በግዜው ተከፍሏል። እንዲሁም ከግል ቁጠባ ወለድ ግብር ብር 47 ሚሊዮን ተከፍሏል።

የተቋሙ የሃብት እና እዳ ዝርዝር መግለጫ

ሰንጠረዥ 3፡- የሃብት እና እዳ ንፅፅር 2016/17 ዓ/ም ከባለፈው ዓመት 2015/16 ዓ/ም

| ርእስ ጉዳይ | ሰኔ 2015/16 ዓ/ም በቢልዮን ብር | | ሰኔ 2016/17 በቢሊዮን ብር | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | እቅድ | ፍፃሜ | እቅድ | ፍፃሜ | ከ 2015/16 ካለ ቀነስ/ ጭማሪ (%) |
| ጠ/ሃብት | 15.57 | 11.96 | 20.59 | 18.772 | 57 |
| ዕዳ | 18.24 | 16.25 | 20.84 | 17.971 | 10.6 |
| ካፒታል | -2.67 | -4.28 | -0.252 | 0.800 | -119 |
| ጥሬ ገንዘብ | 3.77 | 2.57 | 2.79 | 2.499 | -2.8 |
| ትርፍ/ኪሳራ | 0.357 | 1.29 | 1.17 | 0.394 | -69 |
| ጠ/ቁጠባ | 13.089 | 13.915 | 17.106 | 16.11 | 16 |

- ✔ እንደተቋም በዚህ በጀት ዓመት ያለን ጠቅላላ ሃብት ብር 16.46 ቢልዮን እቅድ ተይዞ ፍፃሜ ብር 18.772 ቢልዮን ሊሆን ችሏል። ይህ ከባለፈው የበጀት ዓመት 2015/16 ሲነፃፀር በ 57% ጭማሪ ሊያሳይ ችላል።
- ✔ ዕዳ በዚህ በጀት ዓመት ብር 20.84 ቢልዮን እንዲኖረን እቅድ ተይዞ ፋፃሜ ብር 17.971 ቢልዮን ዕዳ ሊኖረን ችሏል። ይህ አፈፃፀም ከ በጀት ዓመት ሰኔ 2015/16 ጋር ሲነፃፀር በ 10.6% በዚህ በጀት ዓመት የእዳ መጠን ጭማሪ ልያሳይ ችሏል።

- ✔ ካፒታል በዚህ በጀት ዓመት ብር (0.252) ቢልዮን እንዲሆን እቅድ ተይዞ ፍፃሜ ብር 0.800 ቢልዮን ሊሆን ችሏል። ይህ ከባለፈው ዓመት ሰኔ 2015/16 ዓ/ም አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር ከነበረው ነጋቲቭ መጠን ካፒታል በዚህ በጀት ዓመት በ 119% ቅናሽ ሊያሳየን ችሏል።
- ✔ ጥሬ ገንዘብ በእጅና በባንክ ያለው ገንዘብ ሲሆን እቅድ ብር 2.79 ቢሊዮን ሲሆን ፍፃሜ ብር 2.499 ቢሊዩን ሊሆን ችሏል። ይህ ከባለፈው በጀት ዓመት ሰኔ 2015/16 ዓ/ም ፍፃሜ ጋር ሲነፃፀር በ 2.8% ቅናሽ ሊያሳይ ችሏል።
- ✔ የተቋሙ ትርፍ በዚህ በጀት ዓመት በእቅድ ተይዞ የነበረው ብር 1.17 ቢልዮን ሲሆን በ ብሄራዊ ባንክ በተደረገ ማስተካከያ መሰረት ብር 0.394 ቢሊዮን ሊሆን ችሏል። የዚህ በጀት ዓመት ከባለፈው በጀት ዓመት ሰኔ 2015/16 ጋር ሲነፃፀር በ 69% ቅናሽ ሊያሳይ ችሏል።
- ✔ በሌላ በኩል ጠቅላላ ቁጠባ ከባለፈው የበጀት ዓመት ሰኔ 2015/16 ከዚህ ጋር ሲነፃፀር በ16% ሊጨምር ችሏል።

ሰንጠረዥ 4፦ የሃብት እና እዳ መግለጫ (ሰኔ 30, 2025 ዓ/ም/ፈ)

| የሃብት ዓይነት | መጠን/ብሚሊዮን/ | ብፅሒት% |
|---|---|---|
| ጥሬ ገንዘብ እና በባንክ ያለ ገንዘብ | 2,499.76 | 13.37 |
| የሚሰበሰብ ብድር (የተጣራ) | 10,741.57 | 57.46 |
| ተሰብሳቢ ገንዘብ | 3,563.42 | 19.06 |
| አላቂ የቢሮ እቃዎች | 57.53 | 0.31 |
| ቋሚ ንብረት /የተጣራ/ | 562.71 | 3.01 |
| ኢንቨስትመንት | 161.06 | 0.86 |
| ሌሎች | 1,106.76 | 5.92 |
| ድምር | **18,772** | 100 |

ሰንጠረዥ 5፦ ያለን ሃብት ምንጩ በዝርዝር ሲታይ

| Yሃብት ምንጭ | መጠን/በሚሊዮን/ | በ% |
|---|---|---|
| ቁጠባ | 16,117.10 | 86.22 |
| ብድር/ ከባንክ/ | 854.07 | 4.57 |

| | | |
|---|---|---|
| ከማረትና ቀጥታ የገባ | 132.07 | 0.71 |
| የተኸፈለ ካፒታል | 75 | 0.40 |
| እስካሁን ያለ ትርፍ | 403.80 | 2.16 |
| ማቺንግ ፈንድ | 2.49 | 0.01 |
| ሌሎች | 1,108.27 | 5.93 |
| ድምር | **18,772** | 100 |

ፋይናንሻል ትንተና የሚመለከት

የተወሰኑ የፋይናስ መመዘኛዎች በመውሰድ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

✔ ብድር ከ ቁጠባ ያለው ግንኙነት **(Loan to Deposit Ratio)** = ጠ/የተሰጠ ብድር / ጠቅላላ ቁጠባ

= 10.977 / 16.117 = 68%

✔ ሊመለስ የሚችል የተሰጠ ብድር **(Loan and Advance)** በ ብሄራዊ ባንክ የተስተካከለ

የብድር ይዘት **(Capacity Ratio) =** ጠቅላላ የተሰጠ ብድር / ጠቅላላ ሃብት = 10.977 / 18.772 = 58.5%

**በ NBE ሳይስተካከል**

የብድር ይዘት **(Capacity Ratio) =** ጠቅላላ የተሰጠ ብድር / ጠቅላላ ሃብቷ = 10.977 / 13.968 =78.6%

ጠቅላላ ዲፖዚት ሬሾ**/Total Deposit Ratio/** በ ብሄራዊ ባንክ የተስተካከለ

**=** ጠቅላላ ቁጠባ / ጠቅላላ ሃብት = 16.117 / 18.772 = 86%

**በ NBE ሳይስተካከል**

**=** ጠቅላላ ቁጠባ / ጠቅላላ ሃBT = 16.117 / 13.968 = 115%

✔ ልኩዲቲ **(Liquidity Ratio) =** ጥሬ ገንዘብ + በቀላሉ ወደ ገንዘብ ሊቀየሩ የሚችሉ

ጠቅላላ ቁጠባ

= 3.529 = 21.9%
16.11

✔ ካፒታል አዲኪሲ ሬሾ (Capital Adequacy Ratio) በ ብሄራዊ ባንክ የተስተካከለ
= ካፒታል 0.800= 12%
መካከለኛ ክብደት በአደጋ ያለ ብድር 6.667

**3.3.2.** የግዢና ንብረት አስተዳደር

- ✔ በዚህ በጀት ዓመት የተካሄደ ግዢ ሲታይ ቀጥታ 10 ግዜ ፣ በፕሮፎርማ 25 ግዜ በግልፅ ጨረታ ደግሞ 16 ግዜ ግዢ ለመፈፀም እቅድ ተይዞ ፍፃሜው ሲታይ ደግሞ ቀጥታ 10 ግዜ ፣ በፕሮፎርማ 73 ግዜና ግልፅ ጨረታ ደግሞ 31 ግዜን ሊካየድ ችሏል።
- ✔ የግዢና ንብረት አስተዳደር ሁለት መመርያዎች ለማዘጋጀት እቅድ ተይዞ ሁለቱ መመርያዎች ወደሚመለከተው ቀርበው ሊፀድቁ ችሏል።
- ✔ ባለፈው ዓመት ጨረታ ወጥቶላቸው የተገዙና ውል የታሰረላቸው ንብረቶች በተለያየ ምክንያቶች ወደዚህ ዓመት 2017 ዓ/ም ተዛውረው የነበሩት 100 ስዊች ፣ 80 ራውተር ፣ 2 የሴኩሪቲ እቃዎች ፣ 20 ስካነር ፣ 50 የሽልፍ ካፖርድ 50 የሽልፍ ካቢኔት ገቢ ሁኗል።
- ✔ በዚህ በጀት ዓመት የተለያዩ ማህተሞች ፣ ካዝናዎች ፣ ፈርኒቸሮች፣ ጀነሬተሮች ከነ አክሰሰሪ፣ ኤለክትሪክ ሞተር ሳይክል ፣ ሃይብሪድ ሶላር ኢነርጂ ፣ የዋና ቢሮ ጀነሬተር ንብረት ፣ የመኪና መቀያየርያ ስፔሮች ፣ የኤሌክተሮኒክስ እቃዎች ፣ የጀነሬተሮች እና መኪኖች ነዳጅ፣ የንፅህና እቃዎች፣ የ ህትመት ስራዎችና ሌሎች በድምር 57 የንብረት ዓይነቶች በ ብር 124 ሚልዮን ሊገዙ ችሏል።
- ✔ የተቋሙ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ በማካሄድ ሪፖርት ወደሚመለከተው አካል ሊላክ ተደርጓል።
- ✔ በዚህ በጀት ዓመት በተወገደ ንብረት የዋና ቢሮ፣ ዞኖችና ቅርንጫፎች የተገኘ ገቢ ብር 1.232 ሚልዮን ነው።
- ✔ የተሽከርካሪዎች ጥገና በዚህ በጀት ዓመት 59 ግዜ ተደርጓል።
- ✔ በዚህ ዓመት 3 በርዳታ የተገኙ ሞተር ሳይክል ግዝያዊ ታርጋ ፍቃድ እንዲወጣላቸው የተደረገ ሲሆን 21 ለሽልማት አንድ ደግሞ ለአገልግሎት የሚሆን ኤለክትሪካል ሞተር ሳይክል እንዲሁም 10 የኤለክትሪክ ባለ 3 እግር ሞተር ሳይክል በጦርነት ጉዳት ለደረሳቸው ወገኖች ተገዝቶ ተሰጥቶዋቸዋል።
- ✔ የተሽከርካሪዎች ደህንነት ለመጠበቅ የኢንሹራንስ 25 መኪኖች፣ ኢንሹራንስ 30 ሞተር ሳይክል፣ ዓመታዊ ምርመራ ካላውዶ 25 መኪኖች፣ ዓመታዊ ምርመራ ካላውዶ 30 ሞተር ሳይክል ተደርጎላቸዋል።
- ✔ የመኪኖች ጥገና እቅድ 26 ፍፃሜ 26 ፅገና ሊደረግላቸው ተችላል። እንዲሁም 36 ሞተር ሳይክል ለጥገና እቅድ ተይዞ ፍፃሜው 17 ሞተር ሳይክሎች ሊጠገኑ እሏል።

- ✔ የፊልድ መኪና አገልግሎሎት የሚመለከት ደግሞ 47 ግዜ ተጠይቆ 42 መልሲ የተሰጠ ሁኖ የከተማ አገልገሎት ደግሞ በተቀመጠለት አቅጣጫ መሰረት 532 ተጠይቆ 490 ግዜ ለሰጥ ተችሏል።
- ✔ የአገልግሎት ክፍያ የሚመለከት የውሃ ፣ መብራት፣ተሌና ነዳጅ የ ጥገና ብር 7.3 ሚልዩን ክፍያ ሊፈፀም ተችሏል።

### 3.3.3. የኢንጅነሪንግ መደቦች

- ✔ የህንፃ ጥገና የሚመለከት፡- የሽንት ቤት ሃንድ ወሽን ፎሴትን ፣ የውሃ ፍሳሽ ስራዎች፣ የሊፍት ጥገናና ሰርቪስ ማድረግ፣ የእንጨት በር ቁልፎች የመቀየር ስራዎች (ዋና ቢሮ፣ ዓድግራት፣ ማይጨና መኾኒ)፣ የመስታውት እስቲከር (ዋና ቢሮ) ፣ ተሰርቷል።
- ✔ የማንዋሎች እና መመርያዎች መተግበር ፡-የ ኮንስትራክሽን መመርያዎች/ማንዋሎች/, Supervision Manuals, Construction Procurement and Maintenance Manuals የ collateral Estimation Manuales እንዲሁም የቤት ኪራይ ማንዋል ሊሰራ ተደርጓል።
- ✔ ለህንፃ መሳርያ የቀረበ የመሬት ጥያቄ የሚመለከት፡- በተለያዩ ወረዳዎችና ከተሞች ማለትም ዛና ፣ቦራ፣ ሰለዋን፣ ጨርጨር፣ ግጀትና ኣሕስኣ ፕሮፖዛል አዘጋጅተን ሳይት ፕላን/ የዋንነት ማረጋገጫ ካርታ/ ልንረከብ ችለናል።
- ✔ አዲስ ህንፃ ለመስራት በ ግጀት፣ ዛና ፣ ኣሕስኣ G+3 Design በመስራት ወደ ጨረታ ተገብተዋል።

### 3.3.4. የሰው ሃይል አስተዳደር ስራዎች

✔ ተቋማችን በዚህ የበጀት ዓመት ያለው ቋሚ ሰራተኛ ብዛት 3435 ከነዚህ 43% ሴቶች ሁነው ኮንትራት ሰራተኞች ደግሞ 48 ሲሆኑ ከዚህ 4% ሴቶች ናቸው። በድምር የተቋማችን ቋሚና ግዚያዊ ሰራተኛ 3483 ሲሆኑ 42% ሴቶች ናቸው።

- ✔ አዲስ ሰራተኛ በዚህ ዓመት ለመቅጠር እቅድ 306 ፍፃሚ 186 የተቀጠረ ሲሆን ከዚህ 68 ሴቶች ናቸው። በጊዝያዊ የተቀጠሩት 48 ሲሆኑ ከነዚህ 2 ሴቴች ናቸው።
- ✔ የውስጥ እድገት ያገኙ ሰራተኞች ቁጥር 112 ሁነው ከነዚህ 49 ሴቶች ናቸው።
- ✔ በዚህ ዓመት ዝውውር 392 ከነዚህ 170 ሴቶች ሁነው (በፍላጎት 88፣ በተቋሙ ፍላጎት 290፣ በጤና ችግር ምክንያት 14) እንዲዛወሩ ተደርጓል።
- ✔ ከስራ የለቀቁ ሰራተኞች በፍላጎት 54 ፣ በማስተዋቅያ 18፣ በድስፕሊን ምክንያት የተባረሩ 5 ፣ በሞት የተለዩ 13 ፣ በዕድሜ (ጥሮታ) የተሰናበቱ 17 እንዲሁም በተጭበረበረ የትምህርት ማሰረጃ 3 ሲሆኑ በድምር በዚህ ዓመት በጀት ዓመት 110 ሰራተኞች የለቀቁ ሲሆን ከነዚህ 30 ሴቶች ናቸው።
- ✔ ስራ ላይ ያሉ ቅርንጫፎች ብዛት ዞናል 8፣ ደረጃ አንደ ቅርንጫፎች 39 (ከነዚህ 17 ንኡስ ቅርንጫፎች ናቸው፣ ደረጃ ሁለት ቅርንጫፎች 12 ፣ ደረጃ አንድ ን/ቅርንጫፎች 46፣ ደረጃ ሁለት ን/ቅርንጫፎች 121 በድምር ዞናል ጨምሮ 228 ከነዚህ 35 (6 ማይጨው፣ 9 ሽረ እ/ስላሴ ወርቂ ቤት ጨምሮ ፣ 20 ሑሞራ) የደደቢት ተቋሞች ወደ ስራ ያልገቡ አሉ።

- ✔ በቅርቡ ወደ ስራ የገቡ ቅርንጫፎች 7 ሲሆን ዛታ፣ ሓሸንገ፣ ማይማዕዶ፣ ፋላ፣ ታኦ፣ ራያ ኣላማጣ ናቸው።
- ✔ በድስፕሊን የተቀጡ ሰራተኞች በዚህ በጀት ዓመት ሲታይ በፅሑፍ ማስጠንቀቅያ 62፣ የተሰናበቱ 4 ፣ ከሀላፊነት ማውረድ 3 ፣ በገንዘብ ቅጣት 41 በድምር 110 ሰራተኞች የተለያየ ቅጣት ሊያገኙ የተደረገ ሲሆን ከነዚህ 30 ሴቶች ናቸው።
- ✔ የዓመት ዕረፍት በዚህ በጀት ዓመት 2583 ለመስጠት እቅድ ተይዞ ፍፃሜው 1944 ከነዚህ 860 ሴቶች እረፍት ሊሰጣቸው ተችሏል።
- ✔ የስራሕ ልምድና ድጋፍ በሚመለከት ለ563 ሰራተኞች የተሰጠ ሲሆን 1300 ሰራተኞች በተለያየ ግዜ የ ዩዘር ኔም ውክልና ሊሰጥ ተችሏል።
- ✔ ኢንሹራንስ በሚመለከት በዚህ በጀት ዓመት በሞት የተለዩ 5፣ የአካል ጉዳት የደረሳቸው 21 በድምር 26 መኖራቸው ከነዚህ 3 ማስረጃ በማቅረባቸው የተከፈላቸው ሲሆን የተቀሩት 23 የሚገባቸው ጥቅማጥቅም ሙሉ ማስረጃ ባለማቅረባቸው በሂደት ይገኛሉ።

**3.4.** በዋና ስራ አስፈፃሚ ስር የሚገኙ የስራ ክፍሎች የስራ አፈፃፀም የተመለከተ

**3.4.1.** እቅድ ፣ ጥናት እና የቢዝነስ ልማት በተመለከተ

- ✔ የተቋሙ አጠቃላይ የበጀት ዓመት 2016/2017 እቅድ በትግርኛና በ ኢንግሊዘኛ በማዘጋጀት ወደሚመለከተው እንዲቀርብ እና እንዲላክ ተደርጓል።
- ✔ የተጠቓለለ ተቋማዊ ሪፖርት በጀት ዓመት 2015/16፣ 1ኛ ሩ/ዓመት፣ ግማሽ ዓመት ዓመት፣ 9 ወር በጀት ዓመት 2016/17ና ተዘጋጅቷል።
- ✔ ቡብሄራዊ ባንክ የሪፖርት ፎርማት (BSA-Banking Supervision Application) በየሩብ ዓመቱ 4 ግዜ በየወሩ 12 ግዜ የስራ አፈፃፀም ተመልቶ ሊላክ ተደርጓል።
- ✔ ወደ DBE የሚላክ የወዴፕ፣ ታዳሽ ሃይልና ሩፊፕ (WEDP, RUFIP, & REEP) የሚመለከት በየሩብ ዓመቱ እና በየወሩ ሪፖርቶች የተላኩ መሆናቸው።
- ✔ ለሴፍቲኔት አገልግሎት ብድር እና ቁጠባ ለመስጠት የሚያስችል ቢዝነስ ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ወደ MERCY CORPS የተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት (NGO) የተላከ መሆኑ።
- ✔ Enhancing the liquidity of FSP (financial service products) for targeted lending to PSNP households በመሚል ርእስ እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ግብረሰናይ MERCY CORPS ተዘጋጅቶ የተላከ መመሆኑ።
- ✔ **RE&EEP**ና **RUFIP III** የሚመለከቱ ሁለት የቢዝነስ እቅዶች ተዘጋጅተው ወደ DBE የተላኩ መሆናቸው። የቢዝነስ እቅድ ቢዝነስ RE&EEP እቅድ ሁለት ሚልዮን ብር ብድር እንዲፈቀድልን የጠየቅንለት ፕሮፖዛል ሲሆን RUFIP III ደግሞ ከ አንድ ቢልዮን ብር የብድር ጥያቄ ያቀረብንበት የቢዝነስ እቅድ ነው።

ገበያና ተቋማዊ ትስስር የሚመለከት

- ✔ 19 አዳዲስ አማራጮች የብድር እና ቁጠባ ዓይነቶች (13 ዓይነት ቁጠባ፣ 6 የብድር ዓይነት) ያካተተ የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ ወደ ሚመለከተው አመራር ቀርቧል።

- ✔ በብድር እና ቁጠባ የወለድ መጠን ጥናት (Pricing Strategy) ተጠንቶ ወደ አመራር እንዲቀርብ በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት ተደርጓል።
- ✔ 24 ነባር የብድር ላይነቶች ፣ 9 ዓይነት ነባር የቁጠባ ዓይነቶች ለማሻሻል መረጃ በመሰብሰብ የጥናት ሰነድ በማዘጋጀት ሂደት ይገኛል።
- ✔ የደረጃ እድገት የተሰጣቸው (Upgraded) 3 (ተ/ሃይማኖት፣ መርካቶና ሳሪስ) ን/ቅርንጫፎች ኣዲስ ኣበባ ወደ ቅርንጫፎች ያደጉ ሲሆኑ በመመርያ ቁጥር MFI/35/2022 የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ሊያውቃቸው ተደርጓል፣
- ✔ ዳግመ ስያሜ (Renamed) 8 ቅርንጫፎችና ን/ቅርንጫፎች የሰም ማስተካከያ የተደረገላቸው 5 ቅርንጫፎች ( መቐለ ቁ-1 ፣ መቐለ ቁ-2 ፣ መቐለ ቁ-3 ፣ ማይ ወይኒ ፣ ማርያም ኹሓ) እንዲሁም 3 ንኡስ ቅርንጫፎች (እንዳ ጡረታ፣ መቐለ ደቡብ፣ ማይ ኣምበሳ) ሲሆኑ ወደ ብሄራዊ ባንክ የስም ለውጥ ማድረጋችን ለማሳወቅ ልከናል።

### 3.4.2. የሚድያ፣ ሕትመትና ፕሮሞሽን ስራዎች በሚመለከት

- ✔ በሁሉም ዞኖች የተደረገ ዓመታዊ ግምገማ በመገኘት የህዝብ ግንኙነት ስራዎች ተሰርቷል።
- ✔ የተቋሙ የራሱ የፌስ ቡክ ገፅ በመከፈት በስብሰባዎች፣ ስልጠናዎች፣ ሽልማቶች፣ የአዳዲስ ቅርንጫፎች መከፈት ፣ የ30 የስራ ማስታወቅያዎችና 20 ጨረታዎች በመለጠፍ 4,150 እይታና 2,300 ውዴታ ለማግኘት ችሏል።
- ✔ 20 ታፔላ፣ 10 ባነሮች ማሰራት፣ እንዲሁም በሬድዮ እና ቴሌቭዥን እንዲሁም በሪፖርተር ጋዜጣ ተቋማችንን ያስተዋወቅን መሆናችን።

### 3.4.3. የሪስክ እና ኮምፕሊያንስ ስራዎች

- ✔ ሁለገብ የ ሪስክ የመጀመሪያ ደረጃ የዳሰሳ ጥናት በሁሉም ቅርንጫፎቻችን በማካሄድ ግኝቶቹ እና የመፍትሄ ሓሳቦች በመጥመር ወደሚመለከተው ኣካል የቀረበ መሆኑ።
- ✔ የፋይናንሽያልና ኦፕሬሽናል ሪፖርቶች መሰረት በማድረግ ሊኹዲቲ (Liquidity)፣ ካፒታል ኣዲኹየሲ ሬሾን (Capital Adequacy Ratio) ፖርትፎልዮ አት ሪስክን (Portfolio At Risk) በመስራት ተቋማችን ያለበት ደረጃ በየወሩ እየተገመገመ ሪፖርት የሚደረግ መሆኑና እንዲሁም ወደ ALCO ኮሚቴ የሚቀርብ መሆኑ።
- ✔ የተቋሙ Fraud Control and Monitoring Policy ንትካልና በሚመጥን እንዲዘጋጅ የተደረገ መሆኑ።
- ✔ የተቋሙ Anti-Money Laundering and Know Your Customer (KYC) ፖሊሲ ለተቃሙ በሚመች እንዲዘጋጅ የተደረገ መሆኑ።

### 3.4.4. የሕግ አገልግሎት በሚመለከት

- ✔ ውሎችን በሚመለከት፡- 20 በስራ ላይ ያሉ ውሎች ይዘታቸውና ህጋዊነታቸው በመፈተሽ ከነዚህ 10 ውሎች ሊስተካከሉ ተደርጓል በተጨማሪ 3 አዳዲስ ውሎች በ አማርኛ ተዘጋጅተዋል።

- ✔ ሌሎች ሙያዊ አስተያቶች የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮችም 100% ተፈፅሚል።
- ✔ ውዝፍ ብድር በህግ ማስመለስ የሚመለከት ፦ በድርድርና ማስጠንቀቅያ ብር 100.9 ሚልዮን፣ በፎር ክሎዠር ብር 47.3 ሚሊዮን ፣ እንዲሁም በፍርድ ቤት ውሳኔ ብር 9.6 ሚልዮን በአጠቃላይ ብር 157.8 ሚሊዮን በዚህ በጀት ዓመት ሊሰበሰብ ተችሏል።
- ✔ አሰሪና ሰራተኛ በሚመለከት፦ በማይጨው ሰራሕተኛ ተቋሙ ያለ ህጋዊነት አሰናብቶታል በማለት 197 ሺህ ተቋሙ እንዲከፍለው የከሰሰ ሲሆን ፍርድቤቱ ደግሞ ህጋዊነቱ በማረጋገጥ ተቋሙ ትክክል እንደሆነና ለወጣው ወጪ 2000 ብር ለተቋሙ ሰራተኛው መክፈል እንዳለበት በመወሰን ተቋጭቷል።
- ✔ የፍታብሄር መዛግብት በሚመለከት፦ ቀጥታ ክስ 108 ፣ ኣፈፃፀም ክስ 52 ፣ ይግባይ መዝገብ 4 በዚህ በጀት ዓመት መዛግብት ፍታብሄር ነበረ። ይሁን እንጂ በ መቐለ ከጦርነቱ በፊት ተመስርቶ የቆየ 10 ቀጥታ ክስ መዝገብና 11 ኣፈፃፀም ጠቅላላ 21 መዛግብት እስካሁን ሳይንቀሳቀስ የቆመ መዛግብት በመኖራቸው ምክንያታቸው ተጣርቶ እንዲታወቅ መግባባት ተደርሶ የነበረ ሲሆን አድራሻቸው ባለመታወቁ ሊንቀሳቀስ አልቻለም።
- ✔ በኣክሱም ቀጥታ ክስ በብር 370,656 ክስ መስርተን በሂደት ብር 46,332 የተከፈለ ሲሆን መዝገቡ በቀጠሮ ላይ ይገኛል።
- ✔ ከማህበራዊ ዋስትና ጋር ያለን ብር 65 ሚልዮን እንዲመልስልን በሂደት ላይ ያለ መሆኑ።

**3.4.5.** የውስጥ ኦዲት ስራዎች በሚመለከት

- ✔ የኦዲት ኮሚቴ ቻርተር በማዘጋጀት ወደ ቦርድ በመላክና እንዲፀድቅ በማድረግ ወደ ስራ የገባ መሆኑ።
- ✔ በዚህ በጀት ዓመት ቅድመ ኦዲት ለ102 ቅርንጫፎች እና ንኡስ ቅርንጫፎች ለማካሄድ እቅድ ተይዞ ፍፃሜ 98% ቅድመ ኣዲት ሊደረግ ተችሏል።
- ✔ በዚህ በጀት ዓመት ድህረ ኣዲት ለማካሄድ የተያዘ እቅድ 70 ቅርንጫፎች እና ንኡስ ቅርንጫፎች ሲሆን ፍፃሜ 85% ድህረ ኦዲት ሊደረግ ተችሏል። በአቨሬጅ ሲታይ ቅድመና ድህረ ኦዲት 88% ከተያዘው እቅድ ሊፈፀም ችሏል።

**3.4.6.** የደንበኞች ደህንነት ጥበቃና የአገልግሎት አሰጣጥ ክትትል በሚመለከት

- ✔ የተቋሙ የ9 ወር ግምገማ በተደረገበት ግዜ ለሁሉም ዞኖች ፣ ቅርንጫፍና ን/ቅርንጫፍ ማናጀሮች የስራው ይዘት እና በብሄራዊ ባንክ ኢትዮጵያ ክትትል እንደሚደረግለት እና ሪፖርት እንደሚላክለት ግንዛቤ እንዲኖራቸውና የሚነሱ የደንበኞች ቅሬታዎች በፍጥነት መልስ እንዲሰጡ ማብራርያ ተሰጥቷል።
- ✔ በኣዲስ ኣበባ ከሚገኙ ሁለት ባንኮች (ወጋገንና ኣንበሳ) ተሞክሮ በመውሰድ እነዚህ ባንኮች የሚጠቀሙበት የቴክኖሎጂ ዓይነትና አሰራር በመገንዘብ የታየውን ተሞክሮ ወደ ተቋማችን በፅሑፍ የቀረበ ሲሆን እንዲህ ዓይነት አሰራር ወደ ተቋማችን በማስገባት ሊሰራበት ስለሚገባ ከሚመለከታቸው የ አይቲ ባለሙያዎች በመነጋገር ለመስራት በሂደት ይገኛል።

## 4. እንደ ተቋም የነበረን ጠንካራና ደካማ ጎን

### 4.1. ጠንካራ ጎን

- ✔ በሱፐርቪዥንና ድጋፍና ክትትል ከላይ እስከታች በመዋደድ የተሰራ ስራ እና የተፈቱ ችግሮች
- ✔ የደንበኞችየ ሁኔታና የመክፈል አቅም በማጥናት ወደ ስራ ገብተን አመርቂ ውጤት ማምጣታችን
- ✔ በየግዜው ሲነሱ የነበሩ የጥቅማጥቅም ፓኬጆች ወደ ቦርድ ቀርቦ በመፅደቃቸው የሰራተኛው ጥያቄ የተመለሰ መሆኑ

### 4.1.2. ደካማ ጎን

- ✔ አሁንም አዳዲስ ውዝፍ እየተፈጠረ መሆኑ
- ✔ የመንግስት ሰራተኛ ብድሩ አለመመለስ፣
- ✔ ቁጠባ በሚፈለገው መልኩ አለመቆጠብ
- ✔ የተሟላ የሪፖርት ቱል አለመኖር
- ✔ የኢንተግሪቲ ኢሹ አለመፍታት
- ✔ የስነ ምግባር ደንብ አለመተግበር

### 4.1.3. መፍትሄ ሓሳቦች

- ✔ በብድር ማስፋት ላይ በተቻለ መጠን ከተመለሰና ቁጠባ በማሳደግ መስራት።
- ✔ ብድር በጥራት መስጠት ያስፈልጋል
- ✔ ሲስተም ሪፖርት እንዲያወጣ መስራት
- ✔ የቴሌ ሰርቪስ በሌለባቸው እንዲያግዙን ከ ቴሌ ማናጅመንት አካላት ጋር በመነጋገር ችግሮች እንዲፈቱ በማድረግ መስራት።
- ✔ በዲጂታል ስራዎች ተፈጥሮ ያለ መዘናጋት በቦርድና ማናጅመንት ከ ቨንደሮች ጋር በመነጋገር መፍትሄ ማድረግ።
- ✔ ሰራተኛ ከ ዋና ቢሮ የሚተላለፉትን መመርያዎችና አሰራሮች አለመተግበር፣ በቂ ሪዘርቭ ገንዘብ ሳይኖር ብድር መስጠት የመሳሰሉ ችግሮችን የሚፈጥሩ በተቋሙ አሰራር መሰረት አስፈላጊ ቅጣት መስጠት።
- ✔ የሰራተኞች የስነ ምግባር ደንብ እንዲከበር ማድረግ፣

## 4. በእቅድ ተይዘው ያልተፈፀሙ መደቦች

- ✔ የተቋሙ ካፒታል በተለያዩ መንገዶች ለማሳደግ ተይዞ የነበረ እቅድ አልተተገበረም
- ✔ ወርቂ በመግዛት እና በመሸጥ ትርፍ ለማግኘት በውስጣዊ የተቃም ገንዘብ እጥረት እና ውጫዊ አለመረጋጋት ምክንያት አለመሳካቱ፡

## 6. በ በጀት ዓመት 2017/18 ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች

- በውዝፍ ብድር ማስመለስ ላይ ከሚመለከታቸው አካላትና ከመንግስት በመነጋገረ አብሮ ለመስራት ስምምነት ላት መድረስ።
- በሲስተም ላይ ያሉ ችግሮች ከሪፖርት ማውጣት ጀምሮ ሁሉም የሚፈጠሩ ችግሮች የሚፈተቱበተ ሁነቴታ መፍጠር።

- በቀጣይ ሰፊ የብድር ማስመለስና ቁጠባ ማስፋት ከላይ እስከ ታች ጠንካራ ስራ መስራት።
- ተሰብሳቢ ሂሳቦች በመሰብሰብ ገላጭ የሆነ የፋይናንሻል ሪፖርት በመዘጋጀት በትኩረት መስራት።
- በሲስትምና በሌሎች ተቃመማችን የሚፈልጋቸው አዳዲስ አፖች (Ado pay mobile banking, USSD) አሰራሮች በቂ ስልጠና በመስጠት ቴክኖሎጂ የሚውቅ ሰራተኛ በመፍጠር ላይ በትኩረት መስራት።

**6.** አባሪ

| 1.ብድር | | ግብና ፍፃሜ እስከ ሰኔ 30/2025 ዓ.ም.ፈ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ/ቁ | የብድር ዓይነት | ግብ | | ፍፃሜ | | % | |
| | | ሰው | ገንዘብ | ሰው | ገንዘብ | ሰው | ገንዘብ |
| 1 | መደበኛ | 18750 | 1,500,000,000 | 8798 | 1118147868 | 0.47 | 0.75 |
| 2 | ደሞዝተኛ | 3000 | 210,000,000 | 863 | 99352592 | 2.87 | 0.47 |
| 3 | ቲቪቲ | - | - | - | - | - | - |
| 4 | ሕ/ስ/ማ | 150 | 75,000,000 | - | - | - | - |
| 5 | ግብአቶች | - | - | - | - | - | - |
| 6 | ገ/ፓኬጅ | 8000 | 192,000,000 | 2713 | 156330352.7 | 0.34 | 0.81 |
| 7 | ከ/ፓኬጅ | 8700 | 243,600,000 | 757 | 10258682.03 | 0.08 | 0.042 |
| 8 | ዋስትና ፈንድ | 4000 | 800,000,000 | 72 | 1327096.02 | 0.18 | 0.0016 |
| 9 | 3 እግሪባጃጅ ብድር | 200 | 40,000,000 | 3 | 3800000 | 0.015 | 0.095 |
| 10 | ተዘዋዋሪ | - | - | 6 | 900000 | - | - |
| 11 | ቁዴብ | 3000 | 899,400,000 | 125 | 205980000 | 0.41 | 0.22 |
| 12 | ሞዴልና ተሸጋጋሪዎች | 100 | 30,000,000 | 1 | 2000000 | 0.01 | 0.066 |
| 13 | ቢዝነስ | 4500 | 1,800,000,000 | 1255 | 1207967000 | 0.27 | 0.67 |
| 14 | ቤት መስርያ | 6000 | 2,700,000,000 | 688 | 389132831 | 0.11 | 0.14 |
| 15 | ኤለክትሪክ | - | - | - | - | - | - |
| 16 | ኣውድ | 2000 | 400,000,000 | 312 | 159835563.1 | 0.15 | 0.4 |
| 17 | ሊዝ | - | - | - | - | - | - |
| 18 | ሐይል ቆጣቢ | 2000 | 200,000,000 | 499 | 10999973 | 0.24 | 0.054 |
| 19 | የሰራተኛ ብድር | 600 | 60,000,000 | 1246 | 186361002 | 0.41 | 0.31 |
| 20 | እሙን ብድር | 3000 | 450,000,000 | 602 | 144668500 | 0.2 | 0.32 |
| 21 | WOC | 4000 | 400,000,000 | 116 | 72810000 | 0.029 | 0.18 |
| 22 | tech mult | - | - | 5 | 525981 | - | - |
| 23 | wash | 2000 | 160,000,000 | - | - | - | - |
| | ድምር | 70000 | 10,000,000,000 | 18061 | 3,770,397,440.46 | | |

| የብድር አመላለስ አፈፃፀምና ውዝፍ (በብር) |
|---|
| ሰኔ 30/ 2017 ዓ/ም /2025ዓ/ፈ |

| ተ/ቁ | የብድር ዓይነት | የተመለስ ብድር | | | ቀሪ ውዝፍ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እቅድ | ፍፃሜ | በ% ፍፃሜ | እቅድ | ፍፃሜ | ፍፃሜ በ % |
| 1 | መደበኛ | 1,139,530,556 | 729,959,229 | 64.06 | 284,727,857 | 994,898,786 | 28.20 |
| 2 | ደሞዝተኛ | 119,819,751 | 88,388,241 | 73.77 | 43,482,038 | 140,615,658 | 30.92 |
| 3 | ቲቪቲ | - | - | - | - | - | - |
| 4 | ሕ/ስ/ማ | 38,231 | - | - | 27,424 | 37,040 | 74.04 |
| 5 | ግብአቶች | 785,777 | - | - | 563,648 | 42,150 | 1,337.23 |
| 6 | ገ/ፓኬጅ | 231,327,712 | 111,617,478 | 48.25 | 157,730,215 | 325,264,543 | 48.49 |
| 7 | ከ/ፓኬጅ | 237,740,469 | 135,076,154 | 56.82 | 155,497,728 | 408,757,374 | 38.04 |
| 8 | ዋስትና ፈንድ | 139,351,603 | 63,473,022 | 45.55 | 92,296,858 | 261,744,440 | 35.26 |
| 9 | 3 እግር ባጃጅ ብድር | 22,939,373 | 12,831,424 | 55.94 | 16,056,008 | 45,030,257 | 35.66 |
| 10 | ተዘዋዋሪ | 191,979,329 | 31,796,474 | 16.56 | 128,775,083 | - | 1,427.35 |
| 11 | ቋዼፕ | 16,356,576 | 45,330,193 | 277.14 | 5,599,431 | 2,252,486 | 248.59 |
| 12 | ሞዴልና ተሸጋጋሪዎች | 27,886,320 | 28,891,991 | 103.61 | 19,146,916 | 38,060,490 | 50.31 |
| 13 | ቢዝነስ | 532,840,835 | 952,769,757 | 178.81 | 339,045,375 | 948,706,009 | 35.74 |
| 14 | ቤት መስርያ | 1,100,049,888 | 799,114,375 | 72.64 | 247,692,498 | 691,916,140 | 35.80 |
| 15 | ኤሌክትሪክ | 3,331,718 | 4,058,159 | 121.80 | 2,389,885 | 3,044,345 | 78.50 |
| 16 | ኣውድ | 16,106,209 | 62,553,771 | 388.38 | 2,083,428 | 8,099,153 | 25.72 |
| 17 | ሊዝ | 4,168,857 | 531,447 | 12.75 | 2,990,376 | 10,938,738 | 27.34 |
| 18 | ሃይል ቆጣቢ | 3,603,950 | 2,980,236 | 82.69 | 2,020,700 | 5,360,540 | 37.70 |
| 19 | ሰራሕተኛ ልቓሕ | 47,828,595 | 106,342,451 | 222.34 | 3,312,590 | 10,532,399 | 31.45 |
| 20 | እሙን ደንበኛ | 57,863,122 | 70,808,010 | 122.37 | 245,024 | 2,877,805 | 8.51 |
| 21 | Woc | 8,477,796 | 29,000,262 | 342.07 | 2,385,540 | 10,188,783 | 23.41 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 22 | Techno. Multipli | 97,973,333 | 15,981 | - | - | 94,813 | - |
| | ድምር | **4,000,000,000** | **3,275,538,653** | 81.89 | **1,506,068,621** | **3,908,461,950** | 38.30 |

የውዝፍ ንፅፅር

ሰኔ 30/ 2017 ዓ/ም /2025ዓ/ፈ

| ተ/ቁ | የብድር ዓይነት | ሰኔ 2024 የነበረ ውዝፍ | | ሰኔ 30/ 2025 የነበረ ውዝፍ | | ጭማሪ/ቀነስ ውዝፍ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የተበዳሪዎች ብዛት | መጠን ገንዘብ | የተበዳሪዎች ብዛት | መጠን ገንዘብ | ተበዳሪዎች ብዛት | መጠን ገንዘብ |
| 1 | መደበኛ | 68,484 | 1,012,485,085 | 73,061 | 994,898,786 | 4,577 | (2,886,094) |
| 2 | ደመወዝተኛ | 9,802 | 149,819,064 | 9,363 | 140,615,658 | (439) | (9,203,405) |
| 3 | ቲቪቲ | - | - | - | - | - | - |
| 4 | ሕ/ስ/ማ | 14 | 100,260 | 3 | 37,040 | (11) | (63,220) |
| 5 | ግብኣቶች | 42,533 | 2,060,653 | 3,327 | 42,150 | (39,206) | (2,018,502) |
| 6 | ገ/ፓኬጅ | 34,702 | 394,507,033 | 26,101 | 325,264,543 | (8,601) | (69,242,490) |
| 7 | ከ/ፓኬጅ | 13,868 | 493,112,237 | 9,285 | 408,757,374 | (4,583) | (84,354,863) |
| 8 | ዋስትና ፈንድ | 3,684 | 312,168,704 | 2,864 | 261,744,440 | (820) | (50,424,264) |
| 9 | 3 እግረ ባጃጅ ብድር | 438 | 56,037,433 | 3,031 | 45,030,257 | 2,593 | (11,007,176) |
| 10 | ተዘዋዋሪ | 3,124 | 474,543,303 | 1,811 | - | (1,313) | (14,813,352) |
| 11 | ቁዴፕ | 76 | 9,064,987 | 108 | 2,252,486 | 32 | (6,812,502) |
| 12 | ሞዴልና ተሸጋጋሪዎች | 181 | 65,496,019 | 248 | 38,060,490 | 67 | (27,435,529) |
| 13 | ቢዝነስ | 4,389 | 1,176,150,660 | 4,093 | 948,706,009 | (296) | (227,444,651) |
| 14 | የቤት መስርያ | 27,840 | 877,514,549 | 23,497 | 691,916,140 | (4,343) | (185,598,409) |
| 15 | ኤሌክትሪክ | 13 | 7,081,009 | 182 | 3,044,345 | 169 | (4,036,664) |
| 16 | አውድ | 199 | 7,421,030 | 490 | 8,099,153 | 291 | 678,123 |
| 17 | ሊዝ | 144 | 10,928,769 | 151 | 10,938,738 | 7 | 9,970 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 18 | ሓይል ቆጣቢ | 1,851 | 7,141,219 | 1,224 | 5,360,540 | (627) | (1,780,679) |
| 19 | የሰራተኛ ብድር | 729 | 10,294,409 | 976 | 10,532,399 | 247 | 237,990 |
| 20 | እሙን ደንበኛ | 459 | 1,171,550 | 358 | 2,877,805 | (101) | 1,706,254 |
| 21 | Woc | 80 | 8,400,082 | 144 | 10,188,783 | 64 | 1,788,701 |
| 22 | Techno. Multipl | 4 | 35,765 | 4 | 94,813 | - | 59,049 |
| | ድምር | 212,614 | 5,075,533,819 | 160,321 | **3,908,461,950** | (52,293) | (692,641,712) |

| ቀሪ ብድር | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰኔ 30/ 2017 ዓ/ም /2025ዓ/ፈ | | | | | | | |
| ተ/ቁ | ዓይነት ልቓሕ | በዝሒ ቀሪይ ተለቃሕቲ | | | መጠን ቀሪይ ልቓሕ | | |
| | | ትልሚ | ፍፃመ | ብ% ፍፃመ | ትልሚ | ፍፃመ | ብ% ፍፃመ |
| 1 | መደበኛ | 107,808 | 84,618 | 78.49 | 3,348,820,168 | 3,040,107,744 | 90.78 |
| 2 | ደሞዝተኛ | 15,227 | 10,531 | 69.16 | 404,400,379 | 317,419,885 | 78.49 |
| 3 | ቲቪቲ | - | - | - | - | - | - |
| 4 | ሕ/ስ/ማ | 164 | 3 | 1.83 | 75,062,028 | 37,040 | 0.05 |
| 5 | ግብአቶች | 42,533 | 3,327 | 7.82 | 1,274,876 | 42,150 | 3.31 |
| 6 | ገ/ፓኬጅ | 90,240 | 29,848 | 33.08 | 567,315,376 | 495,453,899 | 87.33 |
| 7 | ከ/ፓኬጅ | 38,102 | 12,536 | 32.90 | 629,319,691 | 453,374,729 | 72.04 |
| 8 | ዋስትና ፈንድ | 8,750 | 3,285 | 37.54 | 1,026,089,641 | 272,847,863 | 26.59 |
| 9 | 3 እግሪ ባጃጅ ብድር | 667 | 368 | 55.17 | 77,217,761 | 48,780,483 | 63.17 |
| 10 | ተዘዋዋሪ | 3,529 | 652 | 63.42 | 311,474,979 | 9,021,996 | 2.90 |
| 11 | ቖዴፕ | 3,163 | 139 | 4.39 | 925,937,565 | 174,141,693 | 18.81 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 12 | ሞዴልና ተሸጋጋሪዎች | 297 | 148 | 49.83 | 75,243,886 | 41,556,635 | 55.23 |
| 13 | ቢዝነስ | 10,184 | 5,607 | 55.06 | 3,626,468,470 | 2,639,528,387 | 72.79 |
| 14 | ቤት መስርያ | 35,644 | 24,700 | 69.30 | 4,566,431,077 | 2,650,227,684 | 58.04 |
| 15 | ኤሌክትሪክ | 15 | 7 | 46.67 | 5,405,513 | 3,044,345 | 56.32 |
| 16 | ኣውድ | 3,026 | 1,354 | 44.75 | 426,131,361 | 149,387,561 | 35.06 |
| 17 | ሊዝ | 144 | 151 | 104.86 | 6,763,721 | 10,938,738 | 161.73 |
| 18 | ሃይል ቆጣቢ | 3,963 | 1,745 | 44.03 | 205,847,193 | 16,826,479 | 8.17 |
| 19 | የሰራተኛ ብድር | 1,897 | 2,920 | 153.93 | 137,599,034 | 349,153,885 | 253.75 |
| 20 | እሙን ደንበኛ | 4,083 | 1,508 | 36.93 | 543,879,455 | 227,325,524 | 41.80 |
| 21 | Woc | 4,110 | 258 | 6.28 | 413,754,717 | 77,959,853 | 18.84 |
| 22 | Tech. Multipli | 2,000 | 9 | 0.45 | 62,026,667 | 620,794 | 1.00 |
| | ድምር | 375,546 | 183,714 | 49.34 | 17,436,463,559 | 10,977,797,369 | 62.96 |

**1.Sales/ Income /**

| Dedebit Credit And Saving Institution S.C | | | | |
|---|---|---|---|---|
| sales/ Income | | | | |
| Comparison of Budget & Actual June 31/2025 | | | | |
| **Particulrs** | **Annual budjet** | **Actual** | **Variance** | **Utilizatio n of budget in %** |
| **Interest Income** | | | | |
| Int. earned on loan | 2,443,893,960.61 | 1,755,807,517.27 | -688,086,443.34 | 71.84 |
| Int. earned on deposit | 299,613,008.04 | 194,180,364.92 | -105,432,643.12 | 64.81 |
| **Service Revenue:** | | | 0 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| Commission income | 1,231,667.80 | 3,491,612.23 | 2,259,944.43 | 283.49 |
| Telephone | 334,972.07 | 342,855.65 | 7,883.58 | 102.35 |
| Estimation & Inspection Fees | 2,630,662.80 | 4,575,872.99 | 1,945,210.19 | 173.94 |
| **Other Income:** | | | 0 | |
| Cash Surplus | 873,865.34 | 474,132.15 | -399,733.19 | 54.26 |
| Sales of pass book | 2,537,132.58 | 1,359,268.87 | -1,177,863.71 | 53.58 |
| Penality | 112,865.30 | 235,303.90 | 122,438.60 | 208.48 |
| Sales of bid bond | 46,114.29 | 287,789.88 | 241,675.59 | 624.08 |
| Disposal of old asset | 85,169.58 | 920,481.36 | 835,311.78 | 1,080.76 |
| Office rent | 11,607,861.30 | 8,997,496.33 | -2,610,364.97 | 77.51 |
| Sales of checks & CPO | 29,722.00 | 34,648.39 | 4,926.39 | 116.57 |
| Collected Bad debt | 3,000,000,000.00 | 806,050,538.28 | -2,193,949,461.72 | 26.87 |
| Interest Discount | -79,200,000.00 | -61,521,924.52 | 17,678,075.48 | 77.68 |
| **Sundries** | 4,774,816.69 | 13,482,269.53 | 8,707,452.84 | 282.36 |
| **Gross income** | **5,688,571,818.40** | **2,728,718,227.23** | **-2,959,853,591.17** | |

| **2. Cost of fund/direct cost** | | | |
|---|---|---|---|
| **Dedebit Credit And Saving Institution S.C** | | | |
| **Cost of fund/direct cost** | | | |
| **Comparison of Budget & Actual June 30/2025** | | | |
| **Particulrs** | **annual budjet** | **Actual** | **Variance** |
| **Interest Expense** | | | |
| Interest Paid on Personal Saving | 1,045,250,615.93 | 1,067,921,240.38 | -22,670,624.45 |
| Interest Paid on Group saving | 39,293,848.50 | 27,860,281.85 | 11,433,566.65 |
| Interest Paid Center saving | 1,581,121.72 | 1,017,270.82 | 563,850.90 |
| Interest Paid Time deposit | 5,532,449.06 | 401,367.30 | 5,131,081.76 |
| Interest Paid on borrowing | 252,018,289.72 | 102,342,815.53 | 149,675,474.19 |
| Premium Deposit Insurance | 35,573,640.00 | 40,559,080.00 | -4,985,440.00 |
| 5% Tax on deposit Interest | 15,180,650.52 | 13,222,756.52 | 1,957,894.00 |
| Bad debt expense | 611,337,196.81 | | 611,337,196.81 |
| **Total Cost of fund** | **2,005,767,812.26** | **1,253,324,812.40** | **-476,686,333.23** |

| **3.Salary and Employee benefit Budget** | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **3.Salary and Employee benefit Budget** | | | | |
| **Dedebit Credit And Saving Institution S.C** | | | | |
| **Salary and Employee benefit** | | | | |
| **Comparison of Budget & Actual June 30/2025** | | | | |
| **Particulrs** | **Budgeted** | **Actual** | **Variance** | **Utilization of budget in %** |
| **Clerical & non Clerical Staff salary** | 336,069,682.27 | 501,593,431.71 | -165,523,749.44 | 149.25 |
| Cash Indemnity allowance | 3,785,096.01 | 5,780,619.66 | -1,995,523.65 | 152.72 |
| Medical & Eye Glass | 16,489,496.07 | 26,759,126.81 | -10,269,630.74 | 162.28 |
| Personal Insurance | 7,265.00 | 7,265.00 | 0 | 100 |
| Trainning & Work shop | 241,504.94 | 319,527.29 | -78,022.35 | 132.31 |
| Reward & Prize | 76,629.61 | 84,566.03 | -7,936.42 | 110.36 |
| Education | 783,134.37 | 814,042.97 | -30,908.60 | 103.95 |
| Provident fund 12% & Pension 7% | 37,604,701.28 | 57,375,087.72 | -19,770,386.44 | 152.57 |
| Hard ship allowance | 12,436,415.84 | 16,489,622.78 | -4,053,206.94 | 132.59 |
| Uniform and milk | 4,709,973.63 | 5,215,387.96 | -505,414.33 | 110.73 |
| House Allowance /Acting | 32,685,683.94 | 50,694,307.03 | -18,008,623.09 | 155.1 |
| Mobile Allowanse | - | | 0 | |
| Transport allowance | 43,359,434.81 | 77,091,047.60 | -33,731,612.79 | 177.8 |
| Annual leave pay | 4,539,972.37 | 4,666,910.73 | -126,938.36 | 102.8 |
| Severance Pay | 3,664,651.53 | 4,110,209.44 | -445,557.91 | 112.16 |
| Funeral Expense | 80,130.00 | 82,284.00 | -2,154.00 | 102.69 |
| **Total Salary and Employee benefit** | **496,533,771.67** | **751,083,436.73** | **-254,549,665.06** | 151.27 |

| 4.Adminstration And General expense Budget | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **Dedebit Credit And Saving Institution S.C** | | | | |
| **Adminstration And General expense Budget** | | | | |
| **Comparison of Budget & Actual June 30/2025** | | | | |
| **Particulrs** | **Budgeted** | **Actual** | **Variance** | **Utilization of budget in %** |
| **General expense** | | | | |
| Legal Fee | 836,985.00 | 287,530.48 | 549,454.52 | 34.35 |
| Audit fee | 850,000.00 | 1,920,500.00 | -1,070,500.00 | 225.94 |
| Advertizment and Promotion | 10,256,250.00 | 8,828,934.94 | 1,427,315.06 | 86.08 |
| Cleaning supply | 1,475,400.00 | 996,097.78 | 479,302.22 | 67.51 |
| Entertainment | 3,209,876.73 | 3,132,773.04 | 77,103.69 | 97.6 |
| Inauguration & anniversary | 1,325,516.53 | 1,825,219.15 | -499,702.62 | 137.7 |
| Moter Insurance | 650,000.00 | 742,735.22 | -92,735.22 | 114.27 |
| Moter Examnation Fee | 120,000.00 | | 120,000.00 | - |
| Main.rep.equ.& Furniture | 4,037,250.00 | 1,072,287.51 | 2,964,962.49 | 26.56 |
| Main. & rep.Moter Veh. | 4,265,000.00 | 2,769,637.94 | 1,495,362.06 | 64.94 |
| Main. & rep.building | 706,500.00 | 587,893.16 | 118,606.84 | 83.21 |
| Perdiam & traveling | 29,862,459.60 | 26,757,497.48 | 3,104,962.12 | 89.6 |
| Petrol & oil | 5,099,888.20 | 6,907,710.17 | -1,807,821.97 | 135.45 |
| Stationer & Printing | 21,674,917.81 | 15,822,478.37 | 5,852,439.44 | 73 |
| Postal Service | 390,000.00 | 99,695.37 | 290,304.63 | 25.56 |
| Office rent | 31,905,302.72 | 40,747,773.21 | -8,842,470.49 | 127.71 |
| Subscription | 150,000.00 | 1,380,768.31 | -1,230,768.31 | 920.51 |
| Sundries | 7,399,594.28 | 13,902,052.79 | -6,502,458.51 | 187.88 |
| Tel .Teleg, & telex | 4,779,268.16 | 9,332,026.60 | -4,552,758.44 | 195.26 |
| Wages | 219,999.84 | 1,414,221.64 | -1,194,221.80 | 642.83 |
| Water & light | 372,000.00 | 2,661,760.50 | -2,289,760.50 | 715.53 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| Bank Service Charges | 5,584,556.77 | 3,175,810.42 | 2,408,746.35 | 56.87 |
| Licence fee | 90,000,000.00 | 131,630,355.48 | -41,630,355.48 | 146.26 |
| Transportation | 500,000.00 | 2,087,882.85 | -1,587,882.85 | 417.58 |
| Membership fee | 20,000.00 | 246,000.00 | -226,000.00 | 1,230.00 |
| Depreciation expense | 27,054,855.72 | 37,741,868.11 | -10,687,012.39 | 139.5 |
| Sponsor Ship | 600,000.00 | **9,639,161.00** | -9,039,161.00 | 1,606.53 |
| Consultant fee | 16,000,000.00 | 4,081,134.17 | 11,918,865.83 | 25.51 |
| **Total general expense** | 269,345,621.36 | 329,791,805.69 | 60,446,184.33 | 7,673.73 |

| **Dedebit Credit And Saving Institution S.C** | | | |
|---|---|---|---|
| **Balance Sheet** | | | |
| **Comparison of Budget & Actual June 30/2025** | | | |
| | | | |
| **Particulrs** | **Annual budjet** | **Actual** | **Variance** |
| **ASSETS** | | | |
| **Current Assets:-** | | | |
| Cash | 2,792,399,763.79 | 2,499,760,951.16 | -292,638,812.63 |
| Staff debtor | 95,077,691.21 | 162,261,641.59 | 67,183,950.38 |
| Loans & Advance | 14,550,934,041.15 | 10,977,797,368.57 | -3,573,136,672.58 |
| Allow. For bad debts | -217,107,949.40 | -236,231,683.98 | -19,123,734.58 |
| Investment | 151,000,083.25 | 161,059,900.00 | 10,059,816.75 |
| A/receivable | 1,711,199,196.40 | 3,248,329,273.13 | 1,537,130,076.73 |
| Pre – payment | 75,742,125.80 | 142,986,809.63 | 67,244,683.83 |
| Other than fixed & supplies | 35,974,075.94 | 21,415,816.27 | -14,558,259.67 |
| Office supplies | 76,460,884.94 | 36,117,254.74 | -40,343,630.20 |
| Others | 144,732,565.16 | 1,195,810,451.14 | 1,051,077,885.98 |
| **Total Current Assets** | **19,416,412,478.24** | **18,130,092,587.27** | -1,286,319,890.97 |
| **Fixed Assets:-** | | | 0 |
| Office furniture | 189,841,141.16 | 175,631,420.13 | -14,209,721.03 |
| Office equipment | 45,076,799.43 | 19,268,789.62 | -25,808,009.81 |
| Moter vehicle | 218,232,665.11 | 59,607,007.62 | -158,625,657.49 |
| Buliding | 341,069,716.88 | 284,328,374.82 | -56,741,342.06 |
| Computer | 176,308,705.90 | 178,020,029.86 | 1,711,323.96 |
| Software & Network | 579,130,041.26 | 248,453,878.45 | -330,676,162.81 |
| Accumulated dep, | -374,845,413.81 | -402,599,428.27 | -27,754,014.46 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **Total Fixed Assets** | **1,174,813,655.93** | **562,710,072.23** | -612,103,583.70 |
| **Total Assets** | **20,591,226,134.17** | **18,692,802,659.50** | -1,898,423,474.67 |
| **Liabilities** | | | 0 |
| Current account | 872,862,589.18 | 433,152,174.00 | -439,710,415.18 |
| Personal savings | 15,428,986,010.74 | 14,858,316,642.29 | -570,669,368.45 |
| Group savings | 703,394,195.48 | 660,659,762.43 | -42,734,433.05 |
| Center savings | 22,745,973.42 | 29,225,228.09 | 6,479,254.67 |
| Time depsit | 78,152,035.72 | 135,750,351.99 | 57,598,316.27 |
| Other payable | 1,024,029,687.96 | 487,104,109.80 | -338,219,273.01 |
| Account Payable | 623,510,860.60 | 516,746,031.32 | -198,561,386.56 |
| Long term loan | 2,090,332,303.68 | 850,192,192.30 | -1,236,265,054.49 |
| **Total Liabilities:-** | **20,844,013,656.78** | **17,971,146,492.22** | -2,762,082,359.80 |
| **Capital** | | | 0 |
| Donation Capital Prior Year | 131,564,141.64 | 132,072,641.63 | 508,499.99 |
| Paid up Capital | 10,000,000.00 | 75,000,000.00 | 65,000,000.00 |
| share capital | 500,000,000.00 | 0 | -500,000,000.00 |
| Prior year retained earnings | -2,071,297,868.59 | 199,280,548.48 | 2,270,578,417.07 |
| Net Income (loss) | 1,176,946,204.34 | 394,518,172.41 | -782,428,031.93 |
| **Total Capital** | **-252,787,522.61** | **800,871,362.52** | 1,053,658,885.13 |
| **Total Liab. & Capital** | **20,591,226,134.17** | **18,772,017,854.74** | -1,898,423,474.67 |